2. ሀ) ነህምያ የአመራርን ክህሎት ያሳየው እንዴት ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያንን በክህሎት ስለ መምራት ከነህምያ የምንማራቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

3. ሀ) ራእይ ያለው አመራር ከማስተዳደር ስጦታ እንዴት ይለያል? ለ) እነዚህ ሁለት የተለያዩ ስጦታዎችን የተለያዩ ሰዎች ሲጠቀሙ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) ራእይ ያላቸው መሪዎችና አስተዳዳሪ ዎች ለጤናማ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚያስፈልጉ ግለጽ:: መ) ራእይ ያላቸው ሽማግሌዎች የሚገኙበት ቦርድ እና አስተዳዳሪ ዎች ያሉበት ቦርድ እንዴት እንደሚሠራ አብራራ:: ሠ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቦርዶች የትኛውን ይመስላሉ? ለመልስህ ምክንያትህን ዘርዝር::

4. ሀ) ለአንድ የተለየ አገልግሎት «ራእይ» ያለው አመራር መስጠት ማለት ምን ማለት ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚችሉትን የተለያዩ ራእዮች ዘርዝር:: ሐ) ለአብያተ ክርስቲያናት የአገልግሎት ራእይ መያዝ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? መ) ራእይ ከዕቅድ እንዴት ይለያል? ሠ) ዕቅዶቻችንን ከማውጣታችን በፊት ራእይ ማውጣት ሥራችንን የተሻለ የሚያደርገው እንዴት ነው?

5. ሀ) አማኞች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል «ራእይ» ሊኖራቸው የሚገባው እንዴት ነው? የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ያልሆኑ አማኞች እግዚአብሔር በሥራቸው እንዴት እንዲጠቀምባቸው እንደሚፈልጉ ራእይ ቢያወጡ እንዴት ሊለወጡ እንደሚችሉ ግለጽ:: ለ) ለአገልጋዮች እግዚአብሔርን እንዴት ሊያገለግሉት እንደሚፈልጉ ራእይ ማዘጋጀት ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ:: ሐ) እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር በሥራ ቦታውም ሆነ መንፈሳዊ ስጦታዎቹን በመጠቀም ምን እንዲያደርግ እንደሚፈልግ የግል ራእዮቹን ይናገር::



# ትምህርት ዘጠኝ

## አንደኛ ቀን

ማንም ቢሆን የሚሄድበትን ቦታ ሳያውቅ ፈረስ ላይ አይወጣም፣ ወይም ታክሲ ላይ አይሳፈርም:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ማንኛውም መሪ የት እንደሚወስዳቸው ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት የለበትም:: ሰዎችን በክህሎት ለመምራት የመጀመሪያው እርምጃ ወዴት እንደምንመራቸው ማወቅ ነው:: ዛሬ መሪዎች እግዚአብሔር ሕዝቡን ወዴት እንዲመሩ እንደሚፈልግ ማወቅ እንዳለባቸው የሚያመለክተውን ግልጽ ራእይ የማውጣት ጥናታችንን እንቀጥላለን::

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) የሽማግሌዎች ቦርዳችሁ በራእይ የመምራት ክህሎት ያለው ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ለ) አንተ የቤተ ክርስቲያንህ የሽማግሌዎች ቦርድ ሰብሳቢ ነህ እንበል:: 1) እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችሁ ያለውን ራእይ በመረዳቱ ረገድ ምን ዓይነት ሚና ይኖርሃል? 2) ለቤተ ክርስቲያናችሁ የእግዚአብሔርን ራእይ ለመንደፍ ሌሎች ሽማግሌዎችስ ምን ሚና ይኖራቸዋል? 3) ራእይ በመንደፉ በኩል የአባላትስ ሚና ምን ይሆናል? ረ) ራእዩን በማግለጹና በመወሰኑ ረገድ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምን ሊሆን ይችላል? መሪዎች የግል ፍላጎታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስንም እየሰሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጡት እንዴት ነው?

## ለቤተ ክርስቲያን ራእይ በመንደፉ በኩል የመሪዎች ሚና

1. መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው ራእይ ያለው አመራር መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁለት ዓበይት የመሪነት ሚናዎች አሏቸው::

በመጀመሪያ፣ «ራእይ ያላቸው መሪዎች» ናቸው:: በሕይወታቸው፣ በማስተማር ተግባራቸውና በሚሰጧቸው ውሳኔ ዎች የቤተ ክርስቲያን አባላት የእግዚአብሔርን ፈቃድ

እንዲያውቁና እንዲከተሉ ያደርጋሉ:: ስለሆነም፣ የአገልግሎታቸው ትልቁ ክፍል ቤተ ክርስቲያናቸው እግዚአብሔር ወደሚፈልገው አቅጣጫ እያደገች መሆኗን ማረጋገጥ ነው::

<u>ሁለተኛ</u>፣ መሪዎች «አስተዳዳሪዎችም» ናቸው:: የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎቶች ሕዝቡ የመጨረሻ አቅሙን ተጠቅሞ የሚያከናውናቸውና በሚገባ የሚካሄዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል::

ብዙውን ጊዜ መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን በአግባቡ በማስተ ዳደሩ ተግባር ላይ ስለሚጠመዱ፣ በዚህ ረገድ ብዙ ችግሮች አይከሰቱም:: ይሁን እንጂ፣ መሪዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ አንድ ግልጽ ግብ በመምራት ራእይ ያለው አመራር የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸው እምብዛም በጥልቀት አያስቡም:: እግዚአብሔ ር ሽማግሌዎች በቀዳሚነት የቤተ ክርስቲያኒቱን ጉዳዮች ከማስተ ዳደር ይልቅ፣ ምእመናንን በእረኝነት እንዲያገለግሉና ወደ መንፈሳዊ ዕድገት እንዲወስዱ ይፈልጋል:: የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን «ዲያቆናት» ቤተ ክርስቲያንን የማስተዳደሩን ተግባር እንዲወጡ ነበር ያደረገችው:: ይህም ሽማግሌዎች ከአስተዳደር ሥራው ተላቅቀው ቁልፍ የቤተ ክርስቲያን ተግባራትን እንዲያከናውኑ አስችሏቸዋል (የሐዋ. 6:1-7)::

የሽማግሌዎች ቀዳሚ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንድታከናውን የሚፈልገውን ራእይ እንድትጨብጥ መምራት ነው:: በዚህ ረገድ መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነቶችን ስለሚሰጥ፣ መሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በደንብ ማወቅ ይኖርባቸዋል::

**2. ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያን ራእይ ምንጩ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ራሳቸው አለመሆናቸውን መረዳት አለባቸው::**

ሽማግሌዎች የክርስቶስ አካልን ስለ መምራት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ማወቅ አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ እንጂ እነርሱ አይደሉም:: የቤተ ክርስቲያን ራእይ መምጣት ያለበት ከእርሱ እንጂ ከሽማግሌዎች አይደለም:: የመሪዎቹ ሚና



ዋናው መሪያችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቤተ ክርስቲያን እንድታደርግ የሚፈልገውን ነገር መወሰን፣ እና ከዚያም ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ራእይ እውን እንድታደርግ መምራት ነው:: ሽማግሌዎች ኢየሱስ የሚፈልገውን ነገር በትክክል እንዲያውቁ ሁልጊዜም ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ፣ እግዚአብሔር ለዓለምና ለቤተ ክርስቲያን ባለው ግብ፣ ወዘተ . . . ያለንን መረዳት ማሳደግ አለብን:: ከእግዚአብሔር ቃልና ቀጣይነት ካለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የምናገኛቸው እነዚህ እውነቶች ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ግብ እንድንመራ ያስችሉናል::

**3. አዲስ ኪዳን ስለ ምእመናን እና መሪዎች በሚሰጠው ትምህርት ላይ በመደገፍ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ስቤተ ክርስቲያን ራእይ ስለ መመሥረት ሚናቸው የሚከተሉትን ነጥቦች እንማራለን::**

ሀ. ለቤተ ክርስቲያን ራእይ በመፈለጉ ሂደት ውስጥ ምእመናን በሙሉ መሳተፍ አለባቸው:: ምንም እንኳን ለቤተ ክርስቲያን ራእይ በማዘጋጀቱ በኩል መሪዎች አስፈላጊ ሚና ቢጫወቱም፣ መሪዎች ራእዩን ካዘጋጀን በኋላ ለምእመናን «እንዲህ አድርጉ!» እያልን እናዝዛቸዋለን የሚል አሳብ ከማስተናገድ መጠንቀቅ አለባቸው:: ምእመናንም ሆኑ መሪዎች «የክርስቶስ አካል» በመሆናቸው፣ በራእዩ መስማማት አለባቸው::

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደምትመስል እንድንረዳ ለማገዝ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይጠቀማል:: ከእነዚህ ምሳሌዎች አንዱ ቤተ ክርስቲያን እንደ <u>ቤተሰብ</u> መሆኗን ይናገራል (ዕብ. 2:11):: ኢየሱስ «አባት» የሚለውን ዓይነት ልዩ ስም ከመጠቀም ይልቅ፣ እርስ በርሳችን «ወንድም» ተባብለን እንድንጠራራ ነግሮናል (ማቴ. 23:8-9):: ሐዋርያት በመልእክቶቻ ቸው ውስጥ ብዙውን ጊዜ አማኞችን «ወንድሞች» በማለት ይጠሯቸው ነበር (ዕብ. 3:1፤ ያዕ. 1:16፤ 2ኛ ጴጥ. 1:10):: በእግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አመራር ሥር አማኞች ሁሉ ወንድማማቾችና እኅትማማቾች ናቸው:: በጤናማ ቤተሰብ ውስጥ፣ የቤተሰቡ አባላት አስፈላጊ ጉዳዮችን በጋራ

እንሥተው ይወያያሉ:: ለምሳሌ ያህል፣ «ከክልል ወደ አዲስ አበባ ብንቀየር ጥሩ ነው ወይ?» በሚል ጉዳይ ላይ ትልልቅ ልጆች በሙሉ አሳብ መስጠት ያስፈልጋቸዋል::

ሌላው <u>የአካል ክፍሎች</u> ምሳሌ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ሊሆን፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የዚያ አካል ክፍል ነው (1ኛ ቆሮ. 12:12-27):: እግርና እጅ ኳስን ለመለጋት የአእምሮን ምሪት እንደሚከተሉ ሁሉ፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ራሳችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመራው አገልግሎት ተሳታፊ ነው:: ግለሰቦች የሚሳተፉበት ሁኔታ ሊለያይ ቢችልም፣ ሁላችንም ለእግዚአብሔር ክብር አንድ ነገር ለማድረግ በኢየሱስ ራእይ ላይ ለመሥራት ራሳችንን መስጠት አለብን::

> 2ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ አብዛኞቹ ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎትና ራእይ ለመቀየር ይጥራሉ ወይስ ሽማግሌዎች ውሳኔ ከሰጡ በኋላ ውሳኔዎቹን እንዲያሳውቋቸው ይጠብቃሉ? መልስህን አብራራ:: ለ) ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በጋራ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቀው የሚከተሉባት እንደ አንድ ቤተሰብ ዓይነት መሆኗን ቢያምኑ፣ አመራራቸው እንዴት የሚቀየር ይመስልሃል?

ለ. መሪዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመወሰንና በመረዳት ምእመናንን በማገዙ በኩል ቀዳሚ ሚና ይጫወታሉ:: መንፈስ ቅዱስ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲመሩ መርጧቸዋል (የሐዋ. 20:28ን አንብብ):: በአዲስ ኪዳን፣ ሽማግሌ ዎች ውሳኔ የሚሰጡ መሪዎች አካላት መሆናቸውን እንረዳለን:: ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሰው መመራቷን የሚያሳይ መረጃ አናገኝም:: ስለሆነም፣ ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ለመወሰን ሽማግሌዎች ሁሉ መሳተፍ አለባቸው::

1) ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ <u>መረዳት</u>:: መሪዎች ዓለም የምታከናውነውን ተግባር መመልከት ወይም የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ሥራዎች መከ ረጅ የለባቸውም:: በቀዳሚነት የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: በመሆኑም፣ መሪዎች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጻቸውን



ፍላጎቶቹን ማወቅ አለባቸው:: እግዚአብሔር በአጠቃላይና በተለይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መሪዎችን የሚመራቸው የእግዚአብሔ ር እውነት ነው:: እግዚአብሔር በተለይ ለቤተ ክርስቲያናቸው ምን እንዲያደርጉ እንዲመራቸው መጸለይ አለባቸው:: መሪዎች የመንፈስ ቅዱስ ምሪት በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደ ሆነ በመወያየት ይወስናሉ::

2. የታወቀውን ራእይ ለቤተ ክርስቲያን ምእመናን <u>ግልጽ ማድረግ</u>:: መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ምን እየተናገ ረ እንዳለ ለምእመናን ማስረዳት የሚችሉት እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ ከተገነዘቡ በኋላ ብቻ ነው:: ጳውሎስ እንዳለው፣ ግልጽ መልእክት የማያስተላልፍ መለከት ሰዎችን ለአንድ ተግባር ሊቀሰቅሳቸው አይችልም (1ኛ ቆሮ. 14:8):: በተ መሳሳይ ሁኔታ፣ መሪዎች ያልጠራ ራእይ ብቻ ካላቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ለምእመናን ግልጽ ምስል ሊያስጨብጡ አይችሉም:: ግልጽ ምስል ካላገኙ፣ ምእመናን ስለ ራእዩ ምን ማድ ረግ እንዳለባቸው ወይም እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ ያለውን ዓላማ እንዲፈጽም እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ለማወቅ ይቸገራሉ:: ውሳኔው ከተደረገ በኋላ፣ እያንዳንዱ ሽማግሌ እግዚአብሔር እንዲያከናውኑ ስለ ጠራቸው ተግባር እያንዳንዱ ምእመን እንዲገነዘብና ራእዩን እውን በማድረጉ በኩል ምን ሚና ሊኖረው እንደሚገባ ማሳየት አለበት:: ሽማግሌዎች ራእዩን ግልጽ የማድረጉን ተግባር መቀጠል አለባቸው::

3. ምእመናን ራእዩን ከፍጻሜ ለማድረስ <u>እንዲነሣሡና ይህም መነሣሣት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ</u>:: መሪዎች ራእዩን አንድ ጊዜ ተናግረው ምእመናን ከፍጻሜ እንዲያደርሱት መጠበቅ የለባቸውም:: ምእመናን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ራእይ መታዘዛቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ መሪዎች ሁልጊዜም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ራእይ እንድትታዘዝ ማደፋፈር አለባቸው:: ራእዩን መታዘዝ መጀመሩ አይደለም ዋናው ነገር:: እግዚአብሔርን የሚያስከብረው ራእዩን ተግባራዊ ማድረጉ ነው:: ይህ የመሪዎችንና የምእመናንን ጽናት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው::

በአመዛኙ ቤተ ክርስቲያን ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ ችግሮች ይገጥሟታል። መሪዎች ምእመናን እነዚህን ችግሮች እንዲወጡ ሊያግዟቸውና እግዚአብሔር በሰጣቸው ራእይ ላይ መሥራታቸውን እንዲቀጥሉ ሊያበረታቷቸው ይገባል። ሁልጊዜም ራእዩን መፈጸም ከምእመናን የተፈጥሮ አቅም በላይ ነው። እግዚአብሔር አንድን ግብ የሚሰጠን በተፈጥሯዊ ብቃታችን እንድናከናውን አይደለም። በእኛ ብርታት ሊከናወን የማይችል ነገር እንድናደርግ ይጠይቀናል። ይህም የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም እርሱ እንደሚያስችለን እንድናምን ያደርገናል። እግዚአብሔር የማይቻል በሚመስልበት ጊዜ እንኳን እምነታችንን ይዘን እንድንገኝና እንድንታዘዘው ይፈልጋል። ስለሆነም፣ መሪዎች ምእመናን የእግዚአብሔርን ራእይ እንዲፈጽሙና በታዛዥነት እንዲመላለሱ ሊያበረታቷቸው ይገባል።

ከዚህ እንደምንረዳው፣ እግዚአብሔር አንድ ቤተ ክርስቲያን እንድታደርግ የጠየቃት ተግባር ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ነው። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ራእይ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ራእዩን ተግባራዊ እንድታደርግ የመምራቱን ሚና መጫወት አለባቸው።

ሐ. የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ እንድትጥር የማድረግ ኃላፊነት አለበት። እንደ ዋና መሪነቱ፣ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔ ር ምን እንድታደርግ እንደሚፈልግ እንድታውቅ የመምራት ኃላፊነት አለበት። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት ይችል ዘንድ በግሉ በጥልቀት ለማሰብና በጽናት ለመጸለይ ጊዜ መመደብ አለበት። ሽማግሌዎች በስብሰባው ላይ የተለያዩ ነገሮችን እያነሱና እየጣሉ ጊዜ እንዳያባክኑና ዳሩ ግን ጊዜያቸውን ተጠቅመው የእግዚአብሔርን ራእይ ለማወቅ እንዲጥሩ የሚመራቸው እርሱ ነው። የምርጥ ነገር ጠላት ብዙውን ጊዜ ጥሩ ብቻ በሆነው ነገር መወሰዱ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሽማግሌዎች አነስተኛ ጠቀሜታ ባላቸው ውሳኔዎች መጠመዳቸው የራእይ ጠላት ሊሆንባቸው ይችላል። ምእመናንም ለቤተ ክርስቲያናቸው



የእግዚአብሔርን ራእይ በመወሰኑ በኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድ ረግ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ኃላፊነት ነው። ምንም እንኳን ሰብሳቢው የራእዩ ምንጭ ላይሆን ቢችልም፣ ቤተ ክርስቲያን ራእዩን እውን ለማድረግ እንድትሠራ በመምራቱ በኩል በእግዚአብሔር ፊት ኃላፊነት አለበት። አሳቡን በሚገባ ለመረዳት ስለ ራእዩ በደንብ ማሰብ ያለበትም እርሱ ነው። ራእዩን ከመወሰን ጀምሮ እስከ ማጠናቀቅ ድረስ እርሱ ጠቅላላውን ሂደት ይመራል።

መ. ምንም እንኳን መሪዎች ራእይ በመንደፉ በኩል ምእመናንን ማሳተፍ ቢኖርባቸውም፣ ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ መሪዎች በሚነሡበትና እግዚአብሔር ሕዝቡ ራእዩን እንዲከተል በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ መካከል ብዙውን ጊዜ ክፍተት መኖሩን መ ረዳት አለብን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ሕዝቡ መጀመሪያ ከእግዚአብሔር የመጣውን ራእይ የሚቃወምበት አጋጣሚ መኖሩን እንመለከታለን። ሰዎች አዳዲስ ነገሮችን መጋፈጥ ችግር እንዳያስከትልባቸው ስለሚፈሩ፣ በለመዱት መንገድ መቀጠል ይፈልጋሉ። ምእመናን በጣም ከባድ በሚመስል ጉዳይ ላይ በእግዚአብሔር መታመን ሊከብዳቸው ይችላል። እያንዳንዱ ሰው በራስ-ወዳድነት ስለ ራሱ ፍላጎቶች ብቻ ወደ ማሰቡ ያዘነብላል። ስለዚህ፣ ምእመናን በመጀመሪያ ራእዩን አለመቀበላቸውን በመመ- ልከት፣ መሪዎች ይህ ከእግዚአብሔር የመጣ አይደለም ማለት የለባቸውም። ነገር ግን መሪዎች ራእዩ ከእግዚአብሔር ለመሆኑ እርግጠኞች ከሆኑ፣ ራእዩን በልባቸው ሕያው አድርገው ሊያኖሩት ይገባል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብና ግንዛቤ እንዲለውጥ መጸለይ አለብን። መሪዎች ለሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድና የማይቻል በሚመስልበት ጊዜ እንኳን ፈቃዱን መታዘዝ እንደሚገባ ማስተማር ይኖርባቸዋል። ከዚያም እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብ እስኪለውጥና ራእዩን እስኪቀበሉ ድረስ መጠበቅ አለብን። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ልብ እስኪናገር ሳይጠብቁ በፍጥነት ራእዩን ተግባራዊ ማድረግ ብዙውን ጊዜ ራእዩን ያደናቅፈዋል። ምንም እንኳን ሕዝቡ ሽማግሌዎች ራእዩን እውን እንዲያደርጉ ቢስማሙም፣ ልባቸውን ላይሰጡ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ፣

ምእመናን ለራእዩ እውን መሆን ሙሉ ትብብራቸውን ላያሳዩ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ መሪዎች ምእመናን የማይቀበሉትን ራእይ በግፊት ከሥራ ላይ ለማዋል ይሞክራሉ። በዚህ ጊዜ ምእመናን ስለማይተባበሩ፣ ዕቅዶቹ ውድቅ ይሆናሉ። ምእመናን ገንዘብ ባለመስጠት ወይም ተሳትፎ ባለማድረግ ለሥራው መክናወን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የማያደርጉ ከሆነ፣ ይህ የመሪዎቹን ራእይ እንዳልተቀበሉ የሚያሳይ ግልጽ ምልክት ነው።

ራእዩ የመጣው ከእግዚአብሔር ከሆነ፣ የሕዝቡ ልብ ፈቃዱን እንዲፈልግ ማድረግ የእርሱ ኃላፊነት ነው። ራእዩን እውን ለማድ ረግ የሚያስፈልገውንም ሁሉ ማሟላቱም የእርሱ ኃላፊነት ነው። እንደ መሪዎች፣ ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅዶችን እንድናወጣ እግዚአብሔር ይጠብቅብናል። ይህም እግዚአብሔር ጊዜውንና የሚያስፈልጉትን ነገሮች በሚያዘጋጅበት ጊዜ ዝግጁዎች ሆነን እንድንገኝ ያስችለናል። ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ለመገንባት እግዚአብሔር ጠርቶኛል ብሎ ካመነበት ጊዜ አንሥቶ እግዚአብሔር ነህምያን እንዲያዳምጥ የንጉሡን ልብ እስኪያዘጋጅ ድረስ አራት ወራት ፈጅቷል። ነህምያ እግዚአብሔር ጊዜውን እንዲያዘጋጅ ጠብቋል። በችኮላ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሄዶ ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባትም ራእዩን ሊያደናቅፍ ይችል ነበር። ስለሆነም፣ ትክክለኛውን ጊዜ መጠበቅ ለመሪዎች በጣም አስፈላጊ ነው።

> 3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ምእመናን መጀመሪያ አካባቢ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጠውን ራእይ ሲቃወሙ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) እግዚአብሔር የምእመናንን ልብ በመቀየሩ በራሱ ጊዜ ራእዩ እንዴት እውን ሊሆን እንደ ቻለ አብራራ። ሐ) መሪዎች በምእመናን ላይ የራሳቸውን ራእይ ለመጫን ሲሞክሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ውጤቱ ምን ነበር?

እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ራእይ ያለው መሪና አገልጋይ እንድትሆን ጠርቶህ ከሆነ፣ ሕዝቡን ወዴት እየመራህ ነው? እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚፈልገው ራእይ ወይም አሳብ ከሌለህ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንድታደርስ ወደሚፈልገው ግብ



እየመራህ ላትሆን ትችላለህ። ምናልባትም እያስተዳደርካቸው ትሆናለህ። ራእይ ያለው አመራር ዕድገትንና ለውጥን ያስከትላል። ይህን ለማድረግ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችሁ ያለውን ራእይ በትክክል መረዳት ይኖርብሃል። እግዚአብሔር፣ አንተም ሆንክ መሪ ዎቻችን በሙሉ፣ እርሱ ለቤተ ክርስቲያኖቻቸው የወጠናቸውን አጠቃላይና ልዩ ራእዮች እንድትገነዘቡ እንዲረዳችሁ ጸሎታችን ነው። እንደ ይሳኮር ሰዎች፣ ዘመናችንንና የእግዚአብሔር ሕዝብ ምን ሊያደርግ እንደሚገባ እንዲያውቁ ጸሎታችን ነው። (1ኛ ዜና 12:32 አንብብ።)

## ለሕይወታችን ወይም ለቤተ ክርስቲያናችን ራእይን ለማዘጋጀት የሚያግዙ መሠረታዊ እውነቶች

> 4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በግል ሕይወትህ ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወን የምትፈልጋቸውን ሦስት ነገሮች ዘርዝር። ለግል ሕይወትህ «ራእይን» ማዘጋጀት ለማድረግ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ለማከናወን እንዴት የሚ ረዳህ ይመስልሃል? ለ) ለመጨረሻ ጊዜ የተካፈልከውን የቤተ ክርስቲያን ኮንፈረንስ አስታውስ። መሪዎቹ ኮንፈረንሱን ያዘጋጁበት «ራእይ» ምን ይመስልሃል? መሪዎቹ እግዚአብሔር በመካከላቸው እንዲያደርግ ለሚፈልጉት ነገር ከዚህ የበለጠ ግልጽ «ራእይ» ቢኖራቸው ኖሮ፣ ኮንፈ ረንሱ እንዴት በበለጠ ሊሻሻል ይችል ነበር?

ባለፈው ሳምንት እንደ ተመለከትነው፣ የግልም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ራእይ ለመንፈሳዊ ጤንነታችን አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር በውስጣችንና በመካከላችን ሊያደርግ ስለሚፈልገው ነገር ግልጽ ራእይ ከሌለን፣ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ ብለን ለማደግ እንጥርም። ይህም ሆኖ፣ ብዙዎቻችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእይ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች አንወስድም።

በዚህ ሳምንት ለሕይወታችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ራእይ ለማግኘት ጥረት በምናደርግበት ጊዜ ልናስታውሳቸው የሚገቡን ዓበይት ነጥቦች ምን ምን እንደ ሆኑ እንመለከታለን። በግል ሕይወታችን፣ ወይም መሪዎች ከሆንን ደግሞ፣ በቤተ ክርስቲያናችን ለእግዚአብሔር ክብር አንድ ነገር ለማድረግ

ከፈለግን፣ ለማከናወን የምንፈልገውን ራእይ የምንወስንበት መንገድ ተመሳሳይ ነው:: መሪዎች ነገሮች ባሉበት እንዲቀጥሉ የሚጥሩ ብቻ ሳይሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ለውጥ የሚያመጡ ራእይ ያላቸው እንዲሆኑ የሚያግዙ አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል::

1. እግዚአብሔር መልካም ለውጦችን ለማምጣት ብቃትና ኃላፊነት እንደ ሰጠን ማሰብ አለብን::

በሮሜ 12:1 ጳውሎስ አእምሯችንንና አስተሳሰባችንን መቀየር እንዳለብን ይነግረናል:: ሁላችንም በተፈጥሮ የምናስበው እንደ ዓለማውያን ነው:: ለእግዚአብሔር ክብር የተቻለንን ያህል ምርጥ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንደ መሞከር፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሲሠሩ ያየነውን እንሠራለን:: በአብዛኛው ነገሮች የተሻለ መልክ እንዲይዙ ለመለወጥ ከመጣር ይልቅ፣ ያለንበትን ሁኔታ እንድንቀበል ባሕላችን ያስተምረናል:: ሰዎች ባሉበት ሁኔታ «እጅ እንዲሰጡ» የሚያስተምሩ አንዳንድ ባሕሎች አሉ:: በብዙ ባሕሎች ውስጥ የምንመለከው ምክንያታዊነት፣ «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: ማድረግ የምትችለው ነገር ቢኖር መቀበል ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ከፈቀደው፣ ለምን ለመለወጥ ትሞክራለህ?» የሚል ነው:: በመሆኑም፣ ለሕይወታችን ኃላፊነት እንደ መውሰድ፣ «እግዚአብሔር ከፈቀደ» እንላለን:: ራሳችን ለውጥ ለማምጣት እንደ መሞከር፣ ሁኔታዎች በራሳቸው ጊዜ ይለወጡ እንደ ሆነ ቆመን እንጠብቃለን::

በርግጥ፣ ከእኛ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ እና በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ያሉ ብዙ ነገሮች አሉ:: ነገ በሕይወት መኖር አለመኖራችንን አናውቀውም:: እንደ በሽታና ሞት፣ የእህል መበላሸት ወይም የቤት መቃጠል ዓይነት ነገሮች በየትኛውም ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ በመሆናቸው፣ እነዚህን በተመለከተ ዕቅድ ልናወጣ አንችልም:: በዕቅዳችን ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር እንችላለን ብለን እንዳናስብ መጽሐፍ ቅዱስም ያስጠነቅቀናል (ያዕ. 4:13-16፤ መዝ. 33:10-11):: መጽሐፈ ምሳሌ እንደሚነግረን፣



ምንም እንኳን ሰዎች ቢያቅዱም፣ ውጤቱን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው (ምሳሌ 16:9፤ 19:21)::

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ነገሮች ይለወጡና መልካም ገጽታ ይኖራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለሰዎች ብዙ ኃላፊነትና ብቃት እንደ ሰጣቸው ይነግረናል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች እንመለከታለን:-

1) እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ምድርን እንዲያስተዳድራት የሚጠይቅ ነበር (ዘፍጥ. 1:26-29፤ 2:15):: ይህ ትእዛዝ ሰዎች ዓለምን የሚያጎለብት ወይም የሚያወድም ውሳኔ የማድረግ ብቃት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው:: በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠርን፣ የአንድን ሰው ወይም ነገር ይዘት በምናባችን በመመልከት ለመለወጥ ጥረት ልናደርግ እንችላለን:: እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በዚህ መልኩ ነው:: እግዚአብሔር ለመፍጠር የፈለጋቸውን ነገሮች ሁሉ በምናቡ በመመልከት ነበር ዓለምን የፈጠረው:: ሰዎችም አንድን የተሻለ ነገር በምናባቸው በመመልከት ተግባራዊ የማድረግ ብቃት አላቸው:: የአዳምና ሔዋን በኃጢአት መውደቅ በምንኖርባት ዓለም ላይ በምናመጣው ለውጥ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል:: አሁን የለውጥ ጥረታችንን ከሚያዳክም «እርግማን» ጋር እንታገላለን:: ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ምድርንና የራሳችንን ሕይወት በማስተዋል እንድናስተዳድር የሰጠንን ትእዛዝ አልቀየረውም:: የተወሰኑ መዘዞች እንዳይደርሱብን ነገሮች ከመከሰታቸው አስቀድመን የምናስብበት ብቃት ተሰጥቶናል:: የኤድስ ወይም የጉንፋን በሽታዎች እንዴት እንደሚተላለፉ ስለምናውቅ፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ጥበብ ተጠቅመን ራሳችንን እንድንጠብቅ ይጠብቅብናል:: እንዲሁም ደግሞ ዛፎችን መጨፍጨፍ የአፈርን መሸርሸር በማስከተል ዝናብን እንደሚያዛብ የምንረዳበትን ችሎታ ሰጥቶናል:: ስለዚህ፣ ይህን ችግር ለመከላከልና ጥሩ ዝናብ ለማግኘት እንዲቻል አስቀድሞ ማቀድና ችግሮችን መትከል የእኛ ኃላፊነት ነው::

ምናባቸውን በመጠቀም ወደፊት ነገሮችን ለመለወጥ ማቀድ ከማይችሉ እንስሳት በተቃራኒ፣ በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠርን

የሰው ልጆች ነገሮችንና አኗኗራችንን ለማሻሻል ልናስብ እንችላለን:: አድገት ወይም ልማት የተሻለ ነገር የማለምና ይኸው ራእይ እውን እንዲሆን ተግቶ የመሥራት ውጤት ነው:: ነገሮችን ልንለውጥ አንችልም ብለን ካሰብን፣ መቼም ቢሆን ልናድግ አንችልም:: ሁልጊዜም ከአያት ቅድማያቶቻችን ያልተሻለ ሕይወት ለመግፋት እንገደዳለን::

ከዚህ በታች ሁኔታዎች ከእኛ ቁጥጥር ውጭ ስለሆኑ ነገሮችን ልንለውጥ አንችልም የሚልና ሕይወታችንን ለማሻሻል ነገሮችን ልንለውጥ እንችላለን ብለው የሚያምኑ ሁለት ባሕሎች ተነጻጸረዋል::

| ባህል አንድ:-<br>«ነገሮችን ልንለውጥ አንችልም» | ባህል ሁለት:-<br>«ነገሮችን ልንለውጥና የተሻሉ ልናደርግ እንችላለን» |
|---|---|
| በበሬና በባለ አንድ ማረሻ ሞፈር አርሳለሁ:: ምክንያቱም ሁሌም ስናርስ የነበረው በዚህ መንገድ ነው:: | ብዙ መሬት በቀላሉ ለማረስ እንድችል የተሻለ ሞፈር እሠራለሁ:: ከአንድ በላይ ማረሻ ያለው ሞፈር ወይም ማሽን በመሥራት ብዙ መሬት ለማረስ እሞክራለሁ:: |
| ሁልጊዜም በእግራችን ስንሄድ ወይም በፈረስ ስንጓዝ ኖረናል:: ይኼ በቂያችን ነው:: | ወደምሄድበት አገር ለመድረስ ብዙ ጊዜ ይፈጃል:: በተሻለ ፍጥነት ልጓዝ የምችለው እንዴት ነው? በፍጥነትና በቀላሉ ለመጓጓዝ መኪኖች፣ አውቶቡሶች ወይም አውሮፕላኖች እንሥራ:: |
| ለማገዶም ሆነ ለግንባታ እንጨት ያስፈልገኛል:: ብዙ ዛፎች በአካባቢዬ ስላሉ ሳልጨነቅ የፈለግኩትን ሁሉ መቁረጥ እችላለሁ:: | ዛፎችን ሁሉ ጨፍጭፌ ከጨረስኩ፣ ወደፊት ምን ልጠቀም እችላለሁ? እኔም ሆንኩ ልጆቼ ወደፊት ልንፈልጋቸው ለለምንችል፣ ዛፎችን መትከል ይኖርብኛል:: ምግብ ለማብሰልና ለግንባታ ሌሎች ነገሮችን መጠቀም መቻል አለብኝ:: ብዙ ዛፍ እንዳልፈጅ ኬሮሲን፣ ቡታጋዝ ወይም የመብራት ኃይል መጠቀም አለብኝ:: ለቤት ግንባታም ጡቦችን መሥራት አለብኝ:: |
| ሁልጊዜም የምናመልከው በዚሁ መንገድ ነው:: ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከስብከት በፊትና በኋላ ሁለት ሁለት መዝሙሮችን የሚዘምር ኳየር አላቸው:: እኛም ይህንኑ እናደርጋለን:: | እግዚአብሔር በመንፈስና በእውነት እንድናመልከው ጠርቶናል:: እርሱ ለአማኞች ሁሉ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሰጥቷል:: ስለዚህ እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ለማምለክ ምን ልናደርግ እንችላለን? ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን እንዲጠቀሙ ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው? |



ከዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ ስለ ሁለቱ የአስተሳሰብ ዓይነቶች ግንዛቤ እንዳገኘህ ተስፋ እናደርጋለን:: በባህል አንድ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ነገሮችን ለመለወጥ ሳይሞክሩ ባህላቸው የሰጣቸውን ብቻ ተቀብለው መኖራቸውን ይቀጥላሉ:: ሁኔታዎች ይቆጣጠሯቸዋል እንጂ፣ ያሉባቸውን ሁኔታዎች ለመቆጣጠር አይሞክሩም:: በሌሎች ባህሎች ግን ሰዎች ያሉባቸውን ሁኔታዎች መለወጥ እንደሚችሉ ተረድተዋል:: ስለዚህም የተሻሉ የአስተራረስ ዘዴዎችን፣ ከእግር ወይም ከፈረስ የተሻሉ የመጓጓዣ መንገዶችን፣ እንጨት ከመጠቀም የተሻሉ የምግብ ማብሰያ መንገዶችን ይፈልጋሉ:: በሁለተኛው ባሕል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሁልጊዜም የተሻሉ መንገዶችን ይፈልጋሉ:: አምልኮን ትኩስና አስደሳች በሚያደርግ መንገድ እግዚአብሔርን ለማምለክ ይፈልጋሉ:: በአመዛኙ አንዳንድ ባሕሎች የሚያድጉትና ሌሎች ባሉበት የሚረግጡት ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመለወጥ እንደሚችሉ በማመናቸው ወይም ባለማመናቸው ምክንያት ነው::

እግዚአብሔር እንድናድግና እንድንለወጥ አቅም እንደሚሰጠን የሚያስረዳውን ይህን መሠረታዊ እውነት መረዳት አለብን:: ይህም በዓለም ውስጥ ለውጥ የሚያመጣ ራእይ እንዲኖረንና ይህንኑ ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ እንድንጥር ያስችለናል:: አለዚያ እግዚአብሔር የምናልመውን ራእይ እንዲሰጠን አንጠይቀውም:: ነገሮችን መለወጥ እንደማንችልና ይህንን ማድረጉ የእግዚአብሔር ድርሻ ብቻ እንደ ሆነ ካመንን፣ ዕቅድ ማውጣቱና አንድን ግብ ከዳር ለማድረስ መትጋቱ በፍጹም አስፈላጊ መስሎ ሊታየን አይችልም:: ይልቁንም፣ እግዚአብሔር ሥራውን እንዲያከናውን በማሰብ ቁጭ ብለን እንጠባበቃለን::

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ይህንን አይደለም:: እግዚአብሔር ለክብሩ ዓለምን እንድንለውጥ ኃላፊነት ሰጥቶናል:: ይህን ለማድረግ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድና እንዴት ለውጥ እንድናመጣ እንደሚፈልግ ማወቅ አለብን:: እግዚአብሔር እንድንሆንና እንድናደርግ በሚፈልገው ነገር ሁሉ ከእርሱ ጋር መተባበር አለብን:: የብሉይ ኪዳን ወታደሮች ቁጭ ብለው እግዚአብሔር

እንዲዋጋላቸው አልጠበቁትም። ነገር ግን ድል የሚገኘው በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን እየተገነዘቡ ወጣ ብለው ጠላቶቻቸውን ተዋግተዋል። በእግዚአብሔር ላይ ሲደገፉና በተመሳሳይ ጊዜ ያሉበትን ሁኔታ፣ ለመለወጥ ሲታገሉ፣ እግዚአብሔር ለውጥ ለማምጣት ተጠቅሞባቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር የሚሠራው ፈቃዱን ለማድረግ ስንሻና በኃይሉ ላይ በመደገፍ ያንኑ ራእይ ከፍጻሜ ለማምጣት ስንሞክር ነው።

**5ኛ** ጥያቄ:- ሀ) ከሁለቱ የአስተሳሰብ መንገዶች በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት የሚታየው የትኛው ነው? በከተሞችስ? ለ) ሁልጊዜ በሁኔታዎች ቁጥጥር ሥር ሆኖ ሳይለወጡ ከመኖር ይልቅ ባሕላዊ አስተሳሰብን በመቀየር ነገሮችን ማሻሻልና ነገ የተሻለ ሕይወት ይኖራል የሚል እምነት መያዝ ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ።

2) እግዚአብሔር ሁልጊዜም ስለ ወደፊት በማቀድ ተግባሮቹን ያከናውናል። ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት፣ ኢየሱስ እንደሚሞት ወስኖ ነበር (ራእይ 13:8)። ምንም እንኳን ገና እውን ባይሆንም፣ ለወደፊት የወጠነውን ዕቅድ አሳይቶናል። (የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ።) እኛም የእርሱን ምሳሌነት በመከተል ወደፊት ለማከናወን ስለምንፈልጋቸው ነገሮች ዕቅዶችን ማውጣት አለብን። ነገር ግን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ልዩነት መኖሩ እውነት ነው። እግዚአብሔር አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ሙሉ በሙሉ ነገሮችን ሁሉ ይቆጣጠራል። እርሱ በሉዓላዊነቱ የወደፊት ክስተቶችን ይቆጣጠራል። እኛ ግን ሰዎች እንደ መሆናችን፣ እግዚአብሔር ነገሮችን በመቆጣጠር ዕቅዶቻችንን ተግባራዊ እንዲያደርግልን በእርሱ ላይ እንደገፋለን። ለዚህ ነው፣ «እግዚአብሔር ከፈቀደ» የምንለው (ያዕ. 4:15)። ይህ አባባል ስለ ወደፊት ጉዳዮች ዕቅድ አናወጣም ማለት ሳይሆን፣ በትዕቢት የወደፊት ክስተቶችን እንቆጣጠራለን የማለት አዝማሚያ እንዳይኖረን የሚያስተምረን ነው። እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ከእርሱ ፈቃድ ጋር የሚጣጣሙ ዕቅዶች እንዲፈጸሙ እንዲያደርግ በእርሱ ላይ እንደገፋለን።



6ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ። ያዕ. 4:15፤ መዝ. 20:4፤ ምሳሌ 6:6-11፤ 12:5፤ 13:15፤ 14:8፣ 22፤ 15:19፤ 15:22፤ 20:18፤ 21:5፤ 30:25። ሀ) ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ እንቆጣጠራለን የሚል ትዕቢት እንዳይኖረን እነዚህ ጥቅሶች እንዴት ያስጠነቅቁናል? ለ) ተግቶ መሥራትና ማቀድ ሕይወትን ሊያሻሽል ስለ መቻሉ የተሰጠው ትምህርት ምንድን ነው?

3) መጽሐፈ ምሳሌ ተግቶ መሥራትና ማቀድ ሕይወትን ሊያቀልልን እንደሚችል አያሌ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስተምረናል። አላስፈላጊ ችግሮችን ወደ ሕይወታችን ሊያመጡ ስለሚችሉ መጥፎ ዕቅዶች፣ ምርጫዎችና ስንፍናም ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥተዋል። እንዲያውም፣ መንፈሳዊ «ጥበብ» በሕይወታችን ከፍተኛ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በመከተል ምርጫዎችን ማካሄድ ነው።

እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪነታችን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሰዎች የሚያድጉበትንና የሚለወጡበትን ድባብ መፍጠር አለብን። ያለማቋረጥና ያለ እድገት ተመሳሳይ ነገሮችን ማድረግ የመንፈሳዊ ሕመምና የእምነት ማጣት ምልክት መሆኑን ሁላችንም መማር አለብን። ማደጉን ያቆመ ዛፍ እንደሚሞት፣ እኛም እንዲሁ እንሆናለን። እግዚአብሔር በመካከላችን እንዲሠራ አማኞች ሲያምኑ የሚከሰተውን ለውጥ በደስታ በመቀበል፣ ቤተ ክርስቲያናት በእግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ራእይ ለመቀበል እንዲፈልጉ ማበረታታት አለብን።

ለ. መሪዎች አንድ ለየት ያለ ነገር ባደርግ ሰዎች ይስቁብኛል ከሚለው ፍርሃት ነፃ መውጣት አለባቸው። አንዳንድ መሪዎች፣ ሰዎች ይሳለቁብናል ብለው ስለሚያስቡ፣ አዲስ ነገር ለመጀመር ይፈራሉ። ለየት ብሎ ከመታየት ይልቅ ተመሳስሎ መገኘቱ ይቀላል። ነገር ግን ሸማግሌዎች በዚህ ዓይነቱ አመለካከት ከተጠመዱ እምብዛም ለውጥ ሊመጣ አይችልም። ብዙ መሪዎች የክርስቶስ ባሪያዎች እንደ መሆን የሰዎች አስተሳሰብ ባሪያዎች ይሆናሉ (ገላ. 1:10)።

ሐ. መሪዎች ከዚህ በፊት በቤተ ክርስቲያናቸው ያልተጀመ ረ አዲስ ነገር በሚሞክሩበት ጊዜ ውድቀት እንዳይገጥማቸው ከመፍራት ነፃ መሆን አለባቸው:: መሪዎች አዲስ ነገር ከማይጀምሩባቸው ምክንያቶች ሌላው ውድቀትን መፍራት ነው:: ነገር ግን ያለ ምንም ለውጥ ቁጭ ብሎ ከመኖር ይልቅ አንድን ነገር ሞክሮ መውደቁ የተሻለ ነው:: አይሳካልንም ከሚለው ፍርሃት በላይ ራእይን የሚገድል ነገር የለም:: አንድ የተለየ ነገር ሳይሞክሩ ማደግ አይቻልም:: አምፖል የሠራው ሳይንቲስት በትክክል የሚሠራ አምፖል እስኪያገኝ ድረስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሙከራ ዎች አድርጎ ነበር:: አንድ አምፖል ሞክሮ ሳይሳካለት በቀረ ቁጥር ለምች ይስቁበት ነበር:: እርሱ ግን አንድ ቀን እንደሚሳካለት እርግጠኛ ነበር:: እያንዳንዱ «ውድቀት» በቀጣይነት የተሻለ አምፖል እንዲሠራ ይረዳው ነበር:: የኋላ ኋላ ሙከራው በመሳካቱ፤ እነሆ፣ ዛሬ ሁላችንም በቤታችን ውስጥ መብራት አብርተን ለመጠቀም በቅተናል::

ለእግዚአብሔር በምንሠራበት ጊዜም ተመሳሳይ ነገሮች ይገጥሙናል:: ፈቃዱን ለማወቅ እንድንፈልግና እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ይፈጽመዋል ብለን እንድንታመን ይጠብቅብናል (ፊልጵ. 2:13):: የምንሞክረው ነገር የማይሳካበት ጊዜ ይኖራል:: የሚገርመው ግን፣ ውድቀት ከእግዚአብሔር ዋና ዋና የዕድገት መሣሪያዎች አንዱ ነው:: አንድ ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን አዲስ ነገር ለመጀመር ወይም እግዚአብሔር በአዲስ መንገድ እንዳይመራቸው የሚፈሩ ከሆነ፣ በፍጹም የእግዚአብሔርን ራእይ ሊፈጽሙ አይችሉም:: ሁልጊዜም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለመደውን አሠራር ይዘው ይቆያሉ:: ዕድገት ከሌለ፣ በመጨ ረሻው ላይ መንፈሳዊ ሞት ይከተላል:: በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ሊከሰቱ ከሚችሉ እጅግ አስከፊ ነገሮች አንዱ፣ «ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ነገር ሞክረን አናውቅም» በሚል ሰበብ አዳዲስ ሐሳቦችን መግፋት ነው:: (ማስታወሻ:- ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አንድን ነገር ስላደረጉ ብቻ በችኮላ ለውጥ ማካሄዱም ራሱ አደገኛ ሊሆን ይችላል:: አንዳንድ አዳዲስ ነገሮች ለቤተ



ክርስቲያንና ለምእመናን ጎጂዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ነገሮችን ሁሉ መገምገሙ ጠቃሚ ይሆናል::)

መ. እንደ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች የግል ራእዮች እንዲኖሯቸው ማበረታታት አለብን:: ሽማግሌዎች የራእዮች ምንጭ መሆን አለባቸው ከሚለው አስተሳሰብ መላቀቅ አለብን:: በአብዛኛው እግዚአብሔር ራእይን ለአንድ ሰው ይሰጥና ግለሰቡ ራእዩን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲያመጣው ያደርጋል:: በቢሮክራሲው ውስብስብነት ምክንያት በግለሰቦች ልብ ውስጥ የሚነድደውን የራእይ እሳት ካዳፈንን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመቃወማችን ተጠያቂዎች እንሆናለን:: እንደ መሪዎች ምእመናን ለግል ሕይወታቸውም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ራእዮችን እንዲፈልጉ ማበረታታት አለብን:: እንደ መሪዎች ተግባራችን እግዚአብሔር ለግለሰቦችና ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸው ራእዮች ግልጽ እንዲሆኑ፣ እንዲያድጉና እውን እንዲሆኑ የመሪነትን ሚና መጫወት ነው::

ሠ. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችን የበለጠ ውጤታማ የሚሆንባቸውን መንገዶች መፈለግ አለብን:: እግዚአብሔርን በበለጠ የሚያስከብርና ሕዝቡን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ ልናካሂድ እንችላለን ወይ? እምልኮ በአብያተ ክርስቲያናት ብዙም ለውጥ ሳይደረግበት ከዓመት ዓመት እንዴት እንደሚቀጥል ልብ በል:: ይህንን ማሻሻል የሚቻልባቸው መንገዶች አሉ ወይ? ለማኅበረሰቡ ወንጌሉን በማድ ረሱ በኩል የበለጠ ውጤታማ የምንሆንባቸው መንገዶች አሉ ወይ? ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ምን ልናደርግ እንችላለን? እግዚአብሔር እንደ ግለሰቦችና እንደ ቤተ ክርስቲያን የሰጠንን ራእይ ልንፈጽም የምንችለው እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን ስንጠይቅና ለማደግ ስንፈልግ ነው::

> ፖ ጥያቄ:- ሀ) ባለፉት አሥር ዓመታት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የተ መለከትካቸውን ለውጦች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ለውጦች እንዴት ሊከሰቱ እንደ ቻሉ ግለጽ:: እነዚህ ቤተ ክርስቲያናችሁ ያቀደቻቸው ለውጦች ናቸው ወይስ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተኮረጁ? ሐ) ሰዎች ለማደግና ለመለወጥ ፈቃደኞች እንዲሆኑ ለማገዝ አንድ መሪ ምን ሊያደርግ ይችላል?

2. በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ዕቅዶቻችንን መጀመር አለብን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ መንገዳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ብንሰጥ የተቃና እንደሚያደርገው ይናገራል [ምሳሌ 3:5-6፤ መዝ. (37):5-6]፡፡ ያለ እግዚአብሔር ዕርዳታ ራሳችን የምንፈልጋቸውን ነገሮች እናሳካለን የሚል አሳብ እንዳይኖረን መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል፡፡ ይልቁንም፣ በእግዚአብሔር መታመን አለብን፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች እንደ መሆናችን፣ ለራሳችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ራእይ የማግኘቱን ሂደት መጀመር ያለብን የራሳችንን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመሻት መሆን አለበት (ማቴ. 6:33)፡፡ ሽማግሌዎች ከእግዚአብሔር ክብርና ፈቃድ ውጭ ሌላ ነገር እንደማይፈልጉ መወሰን አለባቸው፡፡ ሁልጊዜም፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ በመጨረሻው የምንከተለው የራሳችንን ሳይሆን ያንተን ፈቃድ ይሆን ዘንድ አባክህን አሳባችንን፣ ውይይቶቻችንንና ፈቃዳችንን አንተ ምራው፡፡ ውሳኔያችን ያንተ ፈቃድ ካልሆነ፣ አንፈልገውም፡፡ በግልጽ ከአንተ አለመሆኑን እንድናውቅ በሩን ዝጋው» ብለው መጸለይ አለባቸው፡፡

ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፣ እኛ ልናደርግ የፈለግናቸውን ነገሮች ካለብን በኋላ እግዚአብሔር እንዲባርካቸው እንጸልይም ማለት ነው፡፡ ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ እንዲገልጥልን እንጠይቀዋለን ማለት ነው፡፡ ምንም እንኳን ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ተከስቶ ሊያዩ የሚፈልጉትን ነገር በተመለከተ የተለያየ አመለካከት ሊኖራቸው ቢችልም፣ በቀዳሚነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጋራ መፈለግ አለባቸው፡፡ ስለሆነም፣ ምንም እንኳን ሽማግሌዎቹ እንዲሆን በሚፈልጉት ነገር ላይ በአሳብ ቢለያዩም፣ እያንዳንዳቸው በጥንቃቄ ሊያዳምጡና፣ «በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?» ብለው ሊጠይቁ ይገባል፡፡ መሪዎች ከራስ-ወዳድነት አመለካከት ሊጸዱና ሰዎች የእነርሱ አሳብ ከሁሉም የተሻለ መሆኑን እንዲያውቁላቸው ለማድረግ ከመጣር እንዲቆጠቡ ያሻል፡፡ መሪዎች የግል ክብር፣ የቤተሰብ ጥቅም፣ ወይም የቤተ ክርስቲያን ክብር ከመሳሰሉት የራስ-ወዳድነት



ፍላጎቶች መራቅ አለባቸው፡፡ የራስ-ወዳድነት መንፈስ ዘው ሲልና ሰዎች ከእግዚአብሔር ፍላጎት በላይ ለራሳቸው ፍላጎት ሲጨነቁ፣ በመሪዎች መካከል ብዙ አለመስማማቶች ይከሰታሉ፡፡

ስለሆነም እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ መጣር ከመጀመራችን በፊትና በኋላ፣ እንዲሁም በሂደቱ ውስጥ መጸለይ፣ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን ነገር ለማወቅ በጣም ጠቃሚ እርምጃ ነው፡፡ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ምእመናኑም በጸሎት (ምናልባትም ከጾም ጋር)፣ ወደ እግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ፈቃዱን ለማወቅ መጣር ይኖርባቸዋል፡፡

> 8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መሪዎች ልባቸውን መመርመራቸውና እግዚአብሔር የሚፈልገውን ብቻ ለማከናወን ራሳቸውን አሳልፈው መስጠታቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) የመሪዎች የራስ-ወዳድነት ፍላጎቶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማግኘት ችግር ሲፈጥሩ የተ መለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ሐ) መሪዎች «ሰዎች ምን ይሉ ይሆን?» በሚለው አሳብ መወጠራቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እንዴት መሰናክል እንደሚሆን ግለጽ፡፡ መ) መሪዎች አንድ ሰው እነርሱ የፈለጉትን ባለማድረጉ ምክንያት መናደዳቸው ከእግዚአብሔር መንግሥት ይልቅ በግል ፍላጎቶቻቸው ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን የሚያሳየው እንዴት ነው?

3. እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማወቅና ለመረዳት በመሻት በትዕግሥት በምንጠባበቀው ጊዜ ራእዩን ይገልጥልናል፡፡

እግዚአብሔር አንድን ነገር ለማድረግ ለሚጣደፍ ሰው ወይም ቡድን እምብዛም ፈቃዱን አይገልጥም፡፡ እግዚአብሔር ረጋ እንድንል ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ነው ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ወደ ተራራ ይወጣ የነበረው፡፡ ኢየሱስ 12ቱን ደቀ መዛሙርት እንደ መምረጥ የመሳሰሉትን ከባባድ ውሳኔዎች ያሳለፈው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ከተገናኘ በኋላ ነበር፡፡ (ሉቃስ 6:12-16ን አንብብ፡፡) በማሰላሰል፣ በመጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናትና ሌሎችን መጻሕፍት በማንበብ በእግዚአብሔር ፊት በጸጥታ ልንቆይ ይገባል፡፡ በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር በልባችንና በአእምሯችን

ላይ ያትማል:: በመሆኑም፣ ለመሪዎች በግልም ሆነ በቡድን እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲገልጽላቸው በጸሎት መጠበቁ አስፈላጊ ነው:: በችኮላ የሚጣደፉ መሪዎች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኒቱ ለክብሩ ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልጉ የማወቅ ዕድል ላይኖራቸው ይችላል:: አሳቦቻችን በራስ-ወዳድነት፣ ቀደም ሲል በተ ያዙት አሳቦች፣ ከዚህ ቀደም በተከናወኑት ተግባራት፣ ወዘተ . . . ሊበረዙ ይችላሉ:: መሪዎች ቢያንስ ቅዳሜና እሑድ ከአካባቢያቸው ፈቀቅ ብለው በመሄድ ምንም ነገር ሳይረብሻቸው ለማሰብ፣ ለመጸለይና ለመነጋገር ቢችሉ መልካም ነው:: መሪዎች በግልና በጋራ የእግዚአብሔርን ቃል ቢያነብቡ፣ ቢጸልዩ፣ ቢያሰላስሉና በአማራጭ አሳቦች ላይ ቢወያዩ፣ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ለመስጠት የሚፈልገውን ራእይ ግልጽ ያደርግላቸዋል::

> **9ኛ ጥያቄ:-** ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች በጸሎት የእግዚአብሔ ርን ፈቃድ ለማወቅ ሞክረው ያውቃሉ? ከሆነ፣ ይህ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዕ ድገት ላይ ያስከተለው አዎንታዊ ለውጥ ምንድን ነው? ለ) መሪዎች አግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያናቸው ምን እንደሚፈልግ በጸሎት ባለመጠየቃቸው የተከሰቱ አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) መሪ ዎች በአንድ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በጸሎት እንዳያሰላስሉ አንቅፋት የሚፈጥርባቸው ምንድን ነው? መ) መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በግልጽ ለማወቅ ምን ለውጥ ሊያደርጉ ይገባል?

## ሁለተኛ ቀን

«ጌታ ሆይ፣ ለቤተ ክርስቲያናችን ራእይ ስጠን» ብለን እንጸልያለን:: ነገር ግን ይህ እውን የሚሆነው እንዴት ነው? አማኞች አጥብቀው ሳይጸልዩና ሳያስቡበት ራእይ ዝም ብሎ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣልን? ትናንት ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ራእይ የሚመጣው እግዚአብሔር በሕይወታችን ወይም በቤተ ክርስቲያናችን ሁኔታዎችን ለመለወጥ የሚያስችል ኃይል እንደሚሰጥ ከማመን መሆኑን ተመልክተናል:: እኛ የሁኔታችን ወይም የባሕላችን ባሪያዎች አይደለንም:: እንዲሁም ደግሞ ሕዝቡ በጸሎትና በጾምታ በሚጠብቀው ጊዜ እግዚአብሔር



ራእይን እንደሚሰጥ ተመልክተናል:: ነገር ግን ውሳኔዎችን ለማካሄድ በምንጣደፍበት ጊዜ፣ «ይህን እንድታደርጉ እፈልጋለሁ!» በማለት አይናገረንም:: ስለሆነም መሪዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በጸጥታ መጠበቅ አለባቸው:: ዛሬ ስለ ራእዮች አንዳንድ መሠረታዊ እውነቶችን መመልከታችንን እንቀጥላለን::

**4. *መሪዎች የእግዚአብሔርን ራእይ ለመወሰን በጋራ መሥራት አለባቸው::***

ራእዩ ከግለሰብ ወይም ከሽማግሌዎች ቢመነጭ ችግር የለውም:: ነገር ግን ራእዩ ምእመናንን በሙሉ ማሳተፍ ካለበት፣ መሪዎች ለሕዝቡ የእግዚአብሔር ራእይ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር የሆነውን ራእይ ለመረዳትና ተግባራዊ ለማድረግ በሚጥሩበት ጊዜ የሚከተሉት ነጥቦች አስፈላጊዎች ናቸው::

ሀ. የሽማግሌዎች ስብሳቢ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ ለመወሰን የሚደረገውን ሂደት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት:: ሰብሳቢው ሁለት ነገሮችን ማድረግ አለበት:: <u>በመጀመሪያ፤</u> እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚፈልገውን ነገር ለማወቅ በግሉ በጸሎትና በማሰላሰል የእግዚአብሔርን ፊት የመፈለግ ኃላፊነት አለበት:: እንደ ሙሴ ወይም ነህምያ፣ ሰብሳቢው የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማትና ፈቃዱን ለማወቅ ንቁ መሆን አለበት:: እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ፈቃዱን በሰብሳቢው ልብ ውስጥ ያስቀምጣል:: እርሱም ከሌሎች ሽማግሌ ዎችና ከምእመናን ጋር በመተባበር ራእዩን ተግባራዊ ያደርገዋል::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሰብሳቢው ራእዩን የመወሰኑንና የማዘጋጀቱን ሂደት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት:: ሽማግሌዎች በቡድን በመጸለይ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማድረግና በመወያየት በአንድነት ለቤተ ክርስቲያናቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ ማድረግ አለበት:: ቤተ ክርስቲያን ሰብሳቢው የፈለገውን የሚወስንባት የአምባገነንነት ስፍራ መሆን የለባትም:: ይልቁንም፣ በእግዚአብሔር የአመራር መዋቅር ውስጥ ያሉ መሪዎች በአንድነት ቤተ

ክርስቲያንን መምራት አለባቸው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማረጋገጡ በኩል ሁሉም ምእመናን መሳተፋቸውን ሰብሳቢው መከታተል አለበት። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን በወጠናቸው ዕቅዶች ላይ ለማስላሰል በቂ ጊዜ ከሰጠ በኋላ፣ ስብሰባዎች መካሄድ አለባቸው። እንዲሁም ሁሉም ራእዩን የሚረዳበትን ተስማሚ ጊዜ መምረጥ አለበት። ሰብሳቢው በጣም ዘገምተኛ ከሆነ፣ ሌሎች ሽማግሌዎችና ሕዝቡ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጠውን ራእይ ትተው የራሳቸውን መንገዶች ሊከተሉ ይችላሉ። በጣም ከፈጠነ ደግሞ፣ በሽማግሌዎችና በምእመናን መካከል የአሳብ መከፋፈል ሊፈጠር ይችላል። እግዚአብሔር የሽማግሌዎቹን ልብ በመንካት ሁሉም በራእዩ ላይ እንዲስማሙ ማድረጉን ማረጋገጥ አለበት። በምእመናንም ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራና ስለ ራእዩ አንድነትን እንዲያመጣ መጠበቅ አለበት። ምእመናን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁና ለመፈጸም ፈቃደኞች እንዲሆኑ ማሳመን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመወሰኑን ሂደት መከታተል የመሪው ኃላፊነት ነው።

ለ. መሪዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመወሰን አብረው መሥራት አለባቸው። እያንዳንዱ ሽማግሌ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን የሚናገረውን መስማት አለበት። እግዚአብሔር ራእዩን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ለማድረግ የሽማግሌዎችን ጥበብና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይጠቀማል። ሰሎሞን እንደ ተናገረው፣ ብዙ አማካሪዎች ባሉበት ስፍራ ትልቅ ጥበብ አለ። (ምሳሌ 11:14 አንብብ።) መሪዎች ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ መወያየታቸው ብዙ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም፣ ይህ አስፈላጊ ሂደት ነው። ሽማግሌዎች ሁሉ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ባለው ፈቃድ ላይ ካልተስማሙ፣ ሦስት ነገሮች ይከሰታሉ።

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ሽማግሌዎች የሚያደርጉት ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን የአንዳንድ ሽማግሌዎች ፍላጎት ለማወቅ ይቸገራሉ። ለእያንዳንዱ ሽማግሌ አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ለማወቅ፣ አርስ በርሳቸው በመነጋገር እግዚአብሔር ፈቃዱን እንደ ገለጠላቸው አርግጠኞች መሆን አለባቸው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ በሽማግሌዎች መካከል መከፋፈል ይፈጠራል። የእግዚአብሔር ዓላማ ሽማግሌዎች እንደ አንድ ቡድን አብረው እንዲሠሩ ነው። መሪዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካልተረዱ፣ ውሳኔዎችን የሚሰጡት በግል ምርጫቸው ላይ በመመሥረት ይሆናል። በግለሰቦች ምርጫዎች መካከል ደግሞ ልዩነቶች ስለሚኖሩ፣ በሽማግሌዎች መካከል ክፍፍል ይኖራል።

<u>ሦስተኛ</u>፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር ራእይ ምን እንደ ሆነ ለምእመናን በግልጽ ለማብራራት ይቸገራሉ። በአንድ ድምጽ በሚናገሩበት ጊዜ፣ ምእመናንን እግዚአብሔር መሪዎቹን ወደ ፈቃዱ እንደ መራቸው ይገነዘባሉ። አንዱ መሪ አንድ ነገር፣ ሌላው ሌላ በሚልበት ጊዜ፣ ሰዎች ግራ ይጋባሉ። በዚህ ጊዜ የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ መሪዎችን አሳቦች ይደግፋሉ። ይህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል እንዲፈጠር ያደርጋል። ምእመናንም በግልጽ ላልተብራራላቸው ራእይ ሕይወታቸውን አይሰጡም።

5. እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸው ራእዮች የአጭርና የረዥም ጊዜ ራእዮችን ያጠቃልላሉ።

ሀ. እግዚአብሔር ለግለሰቦችና ለቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት ራእዮችን ይሰጣል። በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር <u>በአጭር ጊዜ</u> ውስጥ እንድናከናውን የሚፈልጋቸው የአጭር ጊዜ ራእዮች አሉ። እነዚህ የአጭር ጊዜ ራእዮች በተወሰኑ ነገሮች ወይም ቤተ ክርስቲያን በአንድ ወይም በሁለት ዓመታት ውስጥ ለማከናወን በምትፈልጋቸው ነገሮች ላይ ያተኩራሉ። እነዚህ የአጭር ጊዜ ራእዮች በጣም ግልጽ መሆን አለባቸው። «እግዚአብሔር አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ እንድንገነባ ይፈልጋል፣» ወይም «በሁለት ወራት ውስጥ ኮንፈረንስ እናዘጋጃለን፣» የሚሉ ዓይነት የአጭር ጊዜ ራእዮች በሚኖሩን ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ምን ለመፈጸም እንደምንፈልግ መረዳት አለብን። ምን ዓይነት ሕንጻ ነው የምንገነባው? ለምንና እንዴት ነው የምንገነባው? ኮንፈረንስ

የምናዘጋጅ ከሆነ ደግሞ፣ «እግዚአብሔር በዚህ ኮንፍረንስ አማካኝነት ለማከናወን የሚፈልገው ምንድን ነው? እግዚአብሔር የሚፈልገው ለማኅበረሰቡ ፈውስን እንድናመጣ ነው? ለአማኞች ከቃሉ ጠቃሚ እውነቶችን እንድናስተምር ነው? ወይስ ለወንጌል ስርጭት ገንዘብ እንድናሰባስብ?» ራእዩን ለመፈጸም እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ዕቅዶች መወጠን የሚቻለው እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ በትክክል ስናውቅ ብቻ ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ እግዚአብሔር በረዥም ጊዜ ውስጥ እንድንሆን ወይም እንድናደርግ የሚፈልጋቸው <u>የረዥም ጊዜ</u> ራእዮችም አሉ። ይህ፣ «ወንጌል በመላ ኢትዮጵያ ይሰራጭ ዘንድ ምእመናን እምነታቸውን በማካፈልና ገንዘብ በመስጠት ከፍተኛ ተግባር ያከናውናሉ፣» ወይም «እያንዳንዱ ምእመን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያውቃል» የሚሉ ዓይነቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

| |
|---|
| **10ኛ** ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊሰጥ ይችላል የምትላቸውን ሦስት «የአጭር ጊዜ» ራእዮች ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊሰጥ ይችላል የምትላቸውን ሦስት «የረዥም ጊዜ» ራእዮች ዘርዝር። ሐ) ከእነዚህ መካከል እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን በወጠነው ዋንኛ ዕቅድ ውስጥ የበለጠ አስፈላጊ የሆኑት የትኞቹ ናቸው? መ) ብዙውን ጊዜ መሪዎች ትኩረት የሚሰጡት ለየትኞቹ ራእዮች ነው? |

ለ. የአጭር ጊዜ ራእዮች የበለጠ ግልጽነት የሚታይባቸው ሲሆኑ፣ ለመፈጸምም ቀለል ያሉ ናቸው። የረዥም ጊዜ ራእዮች የአጭር ጊዜዎቹን ያህል ግልጽ ያልሆኑና በሚጠናቀቁበት ጊዜ ምን ዓይነት ውጤት እንደሚኖራቸው ለማወቅ የሚከብዱ ናቸው። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ሕንጻ እንድንሠራ የአጭር ጊዜ ራእይ ከሰጠን፣ ብዙውን ጊዜ ይህ ራእይ ግልጽ ሲሆን፣ መሪዎች ራእዩን ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ ለማውጣት አይቸገሩም። ከአንድ ወይም ከሁለት ዓመታት በኋላ ራእዩ ይጠናቀቅና መሪዎቹ በዚህ ራእይ ላይ ማተኮራቸው ያበቃል።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ የሚጠይቅ የረዥም ጊዜ ራእይ ቢሰጥ፣ ይህ



ውስብስብ ራእይ ነው። ብዙውን ጊዜ ለረዥም ጊዜ ራእዮች የተ ግባር ዕቅዶችን ማዘጋጀት ቀላል አይደለም። ለምሳሌ፣ ሰዎች መንፈሳዊ ብስለት ምን እንደ ሆነ ለመረዳትና እንዴት ምእመናንን ወደዚህ ደረጃ ማምጣት እንደሚቻል ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ። ሁላችንም እስክንሞት ድረስ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደጋችንን መቀጠል ስላለብን፣ አንድ ሰው «በመንፈሳዊ ሕይወቱ በሳል ሆኗል» የሚባለው መቼ ነው የሚለውን መወሰኑም አስቸጋሪ ነው። ሰዎች መንፈሳዊ ብስለት እንዲላበሱ ለማገዝ የምናደርጋቸው የተለያዩ ነገሮች አሉ። የማኅበረሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልናካሂድ፣ በጠቃሚ አስተምህሮዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ተ ከታታይ ስብከቶችን ልናቀርብ፣ የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ልናካሂድ፣ ወዘተ . . . እንችላለን። ስለዚህ የረዥም ጊዜ ራእዮችን ለማሳካት የተለያዩ አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ።

ሐ. የረዥም ጊዜ ራእይ ብዙውን ጊዜ የአጭር ጊዜ ፕሮጀክት አይደለም። እግዚአብሔር የአጭር ጊዜ ራእዮችን ይሰጠናል። እነዚህም የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ እንደ መገንባት፣ አዳዲስ የመዘምራን ልብሶችንና የሙዚቃ መሣሪያዎችን መግዛት፣ ወዘተ. . . ናቸው። እነዚህ ነገሮች ግን በቤተ ክርስቲያን ዕድገት ላይ የሚያመጡት የረዥም ጊዜ ለውጥ አይኖርም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድታተኩር የሚፈልጋቸው ብዙ የረዥም ጊዜ ራእዮች አሉት። እነዚህም ለማኅበረሰቡ ወንጌልን ማዳረስ ወይም አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳሎች እንዲሆኑ ደቀ መዝሙር ማድረግ ሊሆኑ ይችላሉ።

መ. ብዙውን ጊዜ ከዘላለማዊ እይታ አንጻር የረዥም ጊዜ ራእዮች «ከአጭር ጊዜ» ራእዮች በላይ አስፈላጊዎች ናቸው። ስለሆነም፣ መሪዎች በአጭር ጊዜ ራእዮች ላይ ከማተኮር ይልቅ የ ረዥም ጊዜ ራእዮችን እውን ለማድረግ የበለጠ ጊዜ መስጠት ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ያህል፣ አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለመገንባት ብንፈልግ፣ ለምእመናን በዚህ የአጭር ጊዜ ራእይ ላይ ትኩረት በማድረግ ገንዘብ ማሰባሰብና ሕንጻውን መሥራት ቀላል ነገር ነው። ነገር ግን የረዥም ጊዜ ራእያችን ምእመናን መንፈሳዊ

ብስለት እንዲያሳዩ ማስቻል ቢሆን፣ ይህንን እውን ለማድረግ ምን ያህል ጊዜ ያስፈልገናል? ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች መምጣታቸው ብቻ እርኪ መስሎ ይሰማናል:: ሰዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ምን ያህል ስለ ክርስቶስ እንደሚመስክሩ ወይም በመንፈሳዊ እውቀታቸው ምን ያህል እያደጉ እንደ ሆነ አናስብም::

ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መሥራቱ ጥሩ ነገር ነው:: ነገር ግን እግዚአብሔር በአማኞች ልብ እንጂ፣ እኛ በሠራነው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ አይኖርም:: (1ኛ ቆሮ. 3:16፤ 6:19-20 እንብብ::) ትልቅ ሕንጸ ልንገነባና በሳል አማኞች ላይኖሩን ይችላሉ:: የእግዚአብሔር ፍላጎት ግን ልጆቹ ሁሉ በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ነው:: ስለሆነም፣ የዓይን ማረፊያ የሚሆን ሕንጸ ከመሥራት ይልቅ፣ በሳል መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸውን አማኞች የመገንባቱ የረዥም ጊዜ ራእይ የበለጠ አስፈላጊ ነው:: ለእግዚአብሔር ክብርን የምናመጣ ዓይነት ሰዎች የሚያደርጉን የረዥም ጊዜ ራእዮች ናቸው:: ምንም እንኳን አንዳንድ ነገሮች ግልጽ ላይሆኑ ቢችሉም፣ መሪዎችና ምእመናን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት የረዥም ጊዜ ራእይ እንድትፈጽም እንደሚፈልግ መረዳታቸው አስፈላጊ ነው:: ከዚያ በኋላ ያንን ራእይ እውን ለማድረግ ዕቅድ ማውጣት ይቻላል::

> 11ኛ ጥያቄ:- ቤተ ክርስቲያን በአጭር ጊዜ ራእዮች በመጠመዷ ይበልጥ አስፈላጊ የሆነውን የረዥም ጊዜ ራእይ ችላ ያለችበትን ሁኔታ ግለጽ::

ሠ. እንደ ግለሰቦች ወይም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በእኛ ደስ የሚለው የረዥም ጊዜ ራእዮቹን በመፈጸማችን ነው:: ጊዜያችንንና ገንዘባችንን ሁሉ ብዙም አስፈላጊ ያልሆኑትን የአጭር ጊዜ ራእዮች ለማከናወን ተግባር ካዋልን፣ ስኬታማ አልሆንንም ማለት ነው:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ የወንጌል ስርጭት ተግባር እንድታከናውን እየፈለገ፣ እኛ ግን ገንዘባችንን ሁሉ ተጠቅመን ሕንጻ ብንገነባና ለመዘምራን ልብስ ብንገዛ፣ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የሆነውን ተግባር ሳናከናውን ቀርተናል ማለት ነው:: መሪዎች እንደ መሆናችን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ዕድገትን በማምጣት ቤተ ክርስቲያን



ይበልጥ አስፈላጊ ወደ ሆነው የረዥም ጊዜ ራእይ እንድትጓዝ ለማድረግ እንችል ዘንድ የምናከናውናቸውን ተግባራት ሁሉ መገምገም አለብን:: መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት በሚገመግሙበት ጊዜ እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ግልጽ እንዲያደርግልን ልንጠይቅና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ራእይ ለመፈጸም ዕቅዶቻችንን ማስተካከል አለብን::

ረ. እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ከረዥም ጊዜ ዕቅዱ ውስጥ ከፊሉን ብቻ ያሳየናል:: (ለምሳሌ፣ አብራምን ከዑር እንዲወጣ ቢጠይቀውም፣ ወዴት እንደሚሄድ አልነገረውም [ዘፍጥ. 12:1]:: ለአብራም ዘሮቹ ከነዓንን እንደሚወርሱ ቢናገርም፣ የተስፋ ቃሉ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ እንደሚፈጸም አልነገረውም [ዘፍጥ. 13:14 -17]):: ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ራእይ ውስንና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈጸም ከሆነ፣ ግልጽ ይሆናል:: አጠቃላይና በረዥም ጊዜ የሚፈጸም ከሆነ ግን፣ ያን ያህል ግልጽ አይሆንም:: ግለሰቦች ወይም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በተወሰነ ጊዜ የገለጠላቸውን ራእይ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ሌሎች እንዲያደርጉ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ደግሞ ይገልጥላቸዋል:: እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ከራእዩ የገለጠላትን ደረጃ ለመፈጸም ዕቅዶችን እንድትወጥን ለማስቻል እያንዳንዱን ደረጃ በግልጽ ያሳያል::

6. ራእይ ከዕቅድ የተለየ ነው:: <u>ራእይ</u> በመጨረሻው ላይ ለማሳካት የምንፈልገው ግብ ነው:: (ማስታወሻ:- አንዳንድ ራእዮች በምድር ላይ ሙሉ በሙሉ እውን አይሆኑም:: ለምሳሌ፣ እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በሳል እንዲሆን ወይም ጠንካራ ወንጌል መስካሪ እንዲሆን:: በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በእነዚህ ግቦች ለናድግ እንኖራለን::) <u>ዕቅድ</u> ራእዩን ለመፈጸም የምናከናውናቸውን ተግባራት የሚያካትት ነው:: ምንም እንኳን ከጊዜ ወደ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተለያዩ ለውጦች ቢከሰቱም፣ የቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና ራእዮች ግን አይቀየሩም:: የሚቀየረው እነዚህን ራእዮች እውን ለማድረግ የምንጠቀምባቸው ዕቅዶች ናቸው::

ብዙውን ጊዜ ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ የምንጠቀምባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። ራእያችን ሳልዳኑት ወንጌልን የምትመሰክር ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን መገንባት ከሆነ፣ የሚከተሉትን ዓይነት ዕቅዶች ልናወጣ እንችላለን። 1) እያንዳንዱ እማኝ እምነቱን እንዲያካፍል የሚረዱ፣ 2) ወንጌላውያንን ወደ ማኅበረሰቡ መላክ፣ እና 3) ወንጌላውያንን ወደ ሌሎች አካባቢዎችና አገሮች መላክ። ጥልቅ ሥር አንድ ዛፍ ማዕበል በተነሣ ጊዜ እንዳይወድቅ እንደሚጠብቀው ሁሉ፣ በአስቸጋሪ ጊዜያትና በባሕሎች ወይም በመሪዎች ለውጥ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ጽናትን የሚሰጣት ራእይ ነው። ጳውሎስ እንደ ተናገረው፣ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ብስለት ያላቸውን ምእመናን የማፍራት ራእይዋን ካሳካች፣ በሐሰተኛ አስተ ምህሮና በሚለዋወጡ አሳቦች ነፋስ አትፍገመገምም (ኤፌ. 4:11-16)። ቤተ ክርስቲያናችሁ ከዚህ የብስለት ደረጃ ላይ ደርሳለች? ካልሆነ፣ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ብስለት ያላቸውን ምእመናን እንድታፈራ እንደሚፈልግ ልታውቅና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ልታደርግ ይገባል።

ራእዩን ካወቅን በኋላ፣ ራእዩን ለማሳካት የተለያዩ መንገዶችን ልንጠቀም እንችላለን። ወደ ራእዩ እየተጓዝን መሆናችንን ለማ ረጋገጥ ነገሮችን የምናከናውንባቸውን መንገዶች መገምገማችንን እንቀጥላለን። ነገሮችን ለማከናወን የሚያስችሉንን ምርጥ ዘዴዎች ለማግኘት ስንል ዕቅዶቻችንን ማስተካከላችንንና መቀየራችንን እንቀጥላለን።

7. ራእዮቻችንንና ዕቅዶቻችንን ለማዘጋጀት ትልቁ መሰናክል የመሪ ዎች ወይም የምእመናን ራስ-ወዳድነት ነው። መሪዎች ለራእዩ የራስ-ወዳድነት አሳብ ሊኖራቸው ይችላል። ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሚያምር ልብስ የለበሱ መዘምራን የሚገኙበት ትልቅ ኳየር እንዲኖራት ትፈልጋለች። ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት «ሌ ሎች ቤተ ክርስቲያኖች ስላላቸው እኛም ያስፈልገናል» የሚል ነው። ወይም ደግሞ፣ «በከተማችን ውስጥ የአገሌ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ሕንጻ ስለ ገነቡ፣ እኛም መገንባት አለብን» ይባላል። ግባችን እግዚአብሔር ከቁም ነገር በማይቆጥራቸው ውጫዊ ነገሮች ላይ



ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር ፉክክር መግጠም አይደለም። ይልቁንም፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመወሰን መፈለግ አለብን። የእግዚአብሔር ሥራ እርሱን ሊያስከብር የሚችለው በትክክለኛ ልባዊ ምክንያቶች የተከናወነ እንደ ሆነ ብቻ ነው። ግለሰቦችን ወይም ቤተ ክርስቲያንን ከፍ ከፍ ለማድረግ ወይም ከሌ ላው በላይ ጎላችንን ለመጥቀም ሲባል በራስ-ወዳድነት ልባዊ ምክንያቶች የተከናወነ ማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን ሊያስከብር አይችልም። ጥሩ አሳብ መስሎ የታየው ነገር ለቤተ ክርስቲያን ተ ጨማሪ ችግሮችን ሊያመጣ ይችላል።

> 12ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብያተ ክርስቲያናት ለተሳሳተ ምክንያት አንድን ነገር ለማድረግ ራእይ ሲያወጡ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) አንድን ነገር በተ ሳሳተ ምክንያት ስናከናውን እግዚአብሔር ደስ የሚለኝ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ።

8. *መሪዎች ዐቢዩን ራእይ በንዑሳን ራእዮች መከፋፈል አለባቸው።*

በአንድ ጊዜ እንድ እንጀራ ሙሉ መጉረስ አይቻልም። አንድ ጊዜ መጉረስ የሚቻለው የተወሰነውን በመቁረስ ብቻ ነው። በተ መሳሳይ ሁኔታ፣ በአጠቃላይ አሳብነት ደረጃ ያለን ራእይ መተግበር አይቻልም። ሰዎች በቀላሉ ይረዱት ዘንድ ራእዩ ወደ ተለያዩ ደረጃ ዎች መከፋፈል አለበት። ለምሳሌ፣ «መንፈሳዊ ብስለት ያለን ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንፈልጋለን» የሚል ትልቅ ራእይ ቢኖረን፣ ለብዙዎች እንዴት ይህ ራእይ ከእነርሱ ሕይወት ጋር እንደሚዛመድ መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በርካታ አነስተኛ «ራእዮች» ቢኖሩን፣ ትልቁ ራእይ ይበልጥ ግልጽ ይሆናል። ስለ ሆነም፣ እንደሚከተለው በንዑሳን ራእዮች ልንከፋፍለው እንችላለን።

ሀ. ወንጌልን ለሰዎች የምናዳርስ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንፈልጋለን።


ለ. እያንዳንዱ ምእመን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቅበትና በመንፈሳዊ ብስለት የሚያድግበት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንፈልጋለን።

ሐ. እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ ስጦታው እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንፈልጋለን፡፡

መ. ምእመናን የክርስቶስን ፍቅር ለእርስ በርሳቸውና ላልዳኑት የሚያሳዩበት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንፈልጋለን፡፡

ከእነዚህ ንዑሳን ራእዮች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል የሆኑ አማኞች የሚገኙባት ቤተ ክርስቲያን የሚለው ራእይ አሁን የበለጠ ግልጽነት ይታይበታል፡፡ እያንዳንዱን ንዑስ ርእስ በቤተ ክርስቲያናችን እውን ማድረግ የሚቻልባቸውን መንገዶች ማሰቡም ቀለል ይላል፡፡

ብዙውን ጊዜ የተለያዩ የራእይ ደረጃዎች በተመሳሳይ ጊዜ ይፈጸማሉ፡፡ አንድን ግለሰብ ወይም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ግብ የሚመራ አንድ ዐቢይ ራእይ ይኖራል፡፡ ዐቢዩን ራእይ ለመፈጸም የሚያግዙ እያሌ ንዑሳን ራእዮችም አሉ፡፡






ለቤተ ክርስቲያን ዐቢይ ራእይ አስፈላጊ ነው፡፡ ለንዑሳን ራእዮች ቅንጅትና ሚዛናዊነትን የሚሰጠው ይኸው ዐቢይ ራእይ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ በሚከተለው ዳያግራም ውስጥ እንደ ተመለከተው፣ የቤተ ክርስቲያን ዓቢይ ራእይ፣ *«ጠንካራ የወንጌል ስርጭት የምታካሂድ፣ በመንፈሳዊ ብስለት የምታድግና ማኅበረሰቡን በፍቅር የምታገለግል ቤተ ክርስቲያን መገንባት»* ነው፡፡ በዚህ ዐቢይ ራእይ ውስጥ ቢያንስ ሦስት ንዑሳን ራእዮች ተደብቀዋል፡፡ በመጀመሪያ፣ የወንጌል <u>ስርጭት</u> ራእይ አለ፡፡ ይህም ምእመናን እምነታቸውን ማካፈልና እንደ ቤተ ክርስቲያንም ወንጌሉን ወደ ሌሎች የዓለም ክፍሎች ማዳረስ እንዳለባቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ የማስተማር ራእይ አለ፡፡ ይህም አማኞች የክርስቶስ በሳል ተከታዮች ይሆኑ ዘንድ በመንፈሳዊ መረዳትና ብስለት ማደጋቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ሦስተኛ፣ ምእመናን ማኅበረሰባቸውን በፍቅር እንዲያገለግሉ የሚጠይቅ <u>የአገልግሎት</u> ራእይ አለ፡፡ (ማስታወሻ:- እነዚህ ንዑሳን ራእዮች በሌሎች ትናንሽ ራእዮች ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ፕሮግራም ለማድረግ የሚፈልጋቸውን ተግባራት የሚያመለክት ራእይ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህም እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ መረዳትና ብስለት እንዲያድግ እንዴት እንደሚረዳ የሚገልጽ ይሆናል፡፡)

እነዚህ ሦስቱም ራእዮች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሚዛናዊነት ይጠብቃሉ፡፡ አንድ ንዑስ ራእይ የዐቢዩን ራእይ ስፍራ ከወሰደ ግን፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሚዛናዊነት ይናጋል፡፡ ለዚህም ነው ብዙውን ጊዜ ጥሩ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት የሚሰጡ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናቻቸው በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ እምብዛም ጥረት የማያደርጉት፡፡ «የወንጌል ስርጭትን» ዐቢይ ራእያቸው ስላደረጉት፣ ሌሎች ራእዮችን ተግባራዊ አያደርጉም፡፡ ስለሆነም፣ ንዑሳን ራእዮችን የሚያስተሳስርና የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎቶች ሚዛናዊነት የሚጠብቅ አንድ ዐቢይ ራእይ መኖር አለበት፡፡

13ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቤተ ክርስቲያን ልትሳተፍባቸው ይገባል የምትላቸውን ንውሳን ራእዮች ዘርዝር። ለ) ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ራእዮች ተግባራዊ ለማድረግ እንደ መሞከር በአንደኛው ላይ ብቻ ትኩረት ብታደርግ አገልግሎቶቿ እንዴት ሚዛናዊነት እንደሚጎድላቸው ግለጽ። ሐ) በ«ሀ» ሥር የዘረዘርካቸውን ንውሳን ራእዮች የሚያስተሳስር ዐቢይ ራእይ ምን ሊሆን ይችላል? መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ዐቢይ ራእይዋን ለምእመናን ለማስረዳት ምን ያህል ጥረት እያደረገች ነው? ሠ) አንተ መሪ ብትሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎቶች ሚዛናዊ በሆነና በተቀናጀ መንገድ እንዲካሄዱ ዐቢይና ንውሳን ራእዮችን ለምእመናን ለማሳወቅ ምን ታደርግ ነበር?

**9. መሪዎች አንድን ተግባር የሚፈጽሙበት ምክንያት እግዚአብሔርን የሚያስከብር መሆኑን መገምገም አለባቸው።**

እግዚአብሔርን የሚያስከብር ዕቅድ ማውጣት ማለት ለተግባር ያነሣሡንን ልባዊ ምክንያቶች መገምገም ጭምር ነው። እግዚአብሔር የሚመለከተው ምን ማድረጋችንን ብቻ ሳይሆን፣ ለምን ብለን ያንን ተግባር እንደ ፈጸምን ጭምር ነው። ራእያችን ለራሳችን እና ለቤተ ክርስቲያናችን ክብርን የሚያመጣ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ደስ አይለኝም፣ አገልግሎታችንንም አይባርከውም። ዓላማችን ሁልጊዜም መንግሥቱን በማስፋፋት ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት ሊሆን ይገባል። ራእይ በማውጣቱ ሂደት ውስጥ፣ *«እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ ይፈልጋል? ይህንን የምናደርገው ለምንድን ነው? ይህ ጊዜያችንንና ትኩረታችንን በቀዳሚነት መስጠት ያለብን ነገር ነው?»* የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን። (ሰዎች እንዴት በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ለተሳሳተ ምክንያት ራእይ ሊያዘጋጁ እንደሚችሉ የሚያሳየውን ክፍል ከታች እንመለከታለን።)

14ኛ ጥያቄ:- መሪዎች ጥሩ ራእይ ሊኖራቸውና ራእዩ የተነደፈበት ምክንያት የተሳሳተ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ግለጽ።

**10. መሪዎች ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለራእዩ ማረጋገጫ ማግኘት አለባቸው።**



ምእመናን እንደ ራሳቸው ሳይቀበሉት መሪዎች ብቻ የወሰኑት ራእይ እውን ሊሆን አይችልም። የመሪዎች ራእይ ብቻ ሆኖ ከቀረ፣ ምእመናን መሪዎቹ ሥራውን እንዲያካሂዱ ይጠብቃሉ። ብዙውን ጊዜ መሪዎቹ በጣም ከተጫኗቸው በኋላ በሥራው ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። ነገር ግን ምእመናን ራእዩ የሁሉም ሰው እንደ ሆነና ይህ እግዚአብሔር እንዲያከናውኑ የሚፈልገው ተግባር እንደ ሆነ ካመኑ፣ በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር ይሠራሉ። የመንፈሳዊ አመራር ቁልፉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያዳምጡና እንዲታመኑበት መርዳት ነው። ምእመናን መሪዎችን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን እየታዘዙ መሆናቸውን ማመን አለባቸው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሥራው የመገናኛውን ድንኳን ግንባታ ሊመስል ይችላል። ሕዝቡ ከሙሴ ጋር ለእግዚአብሔር ቤት በመሥራታቸው እጅግ ደስ ተሰኝተው ስለ ነበር፣ በፈቃደኝነት እጅግ ብዙ ነገሮችን ሰጡ። ከሚገባው በላይ በመስጠታቸው ሙሴ «በቃችሁ» በማለት ስጦታዎቹን ማስቆም አስፈልጎት ነበር። (ዘጸአ. 36:1-7ን አንብብ።)

መሪዎች እነርሱ የእግዚአብሔር ራእይ ነው ብለው የተቀበሉትን እሳብ ምእመናን እንዲቀበሉ ጫና ማሳደር የለባቸውም። መሪዎች ሕዝቡን በዚህ ዓይነት ማሳመን ካለባቸው፣ አንድም ራእዩ ከእግዚአብሔር አይደለም፣ ወይም ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ ጊዜው አልደረሰም ማለት ነው። ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ በሰዎች ልብ ውስጥ መሥራት የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነው። ይህ የመሪዎች ኃላፊነት አይደለም። መሪዎች በሕዝቡ ላይ ጫና አሳድረው «እሺ» ቢያሰኙአቸው እንኳን፣ በሙሉ ልባቸው ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ አይሞክሩም።

በአብዛኛው መሪዎች የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በሚጥሩበት ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ከምእመናን ይሰውራሉ። አንዳንድ መሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ጥሩ ነገሮች ብቻ ይነግሯቸዋል። ነገር ግን ኢየሱስ እርሱን ቢከተሉ ስለሚያጋጥማቸው መስቀልና ስደት ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ተናገረ ሁሉ፣ ምእመናን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚፈጽሙበት ጊዜ ሊገጥማቸው የሚችለውን ችግር መግለጽ ተገቢ ነው።

መሪዎች ለምእመናን ማቅረብ ያለባቸው እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ የሚያሳየውን ራእይ ብቻ ሳይሆን፣ ግልጽ ሆኖ የተዘጋጀ ዕቅድ ጭምር ነው:: ምእመናን ራእዩን ካጸደቁ በኋላ፣ እያንዳንዱ ሰው በራእዩ ውስጥ ምን ድርሻ እንደሚኖረው ማወቅ አለበት:: አለዚያ ምእመናን በሥራው ላይ ፍላጎት አይኖራቸውም:: ለሜታቸው ስለሚቀዘቅዝ፣ መሪዎች እንደገና ለሥራው ለማነሣሣት ይቸገራሉ:: መጀመሪያውኑ በሥራው ላይ እንዲያተኩሩ ማድረጉ ከዚህ ይልቅ ከባድ ነው:: ስለሆነም፣ መሪዎች በተቻለ ፍጥነት ሕዝቡ በሥራው ላይ እንዲያተኩር ቢያደርጉ መልካም ነው:: እያንዳንዱ ምእመን ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ ምን መሥራት እንዳለበት የሚያመለክት ዕቅድ ማውጣት አለባቸው::

11. እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን ራእይ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ራእዩን ለመፈጸም የሚያስፈልጉትንም ነገሮች ጭምር እንደሚሰጣቸው ቃል ይገባላቸዋል::

መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ራእይ እንዲፈጽም እናንቀሳቅሰዋለን:: ለሁኔታዎች ብቻ ምላሽ መስጠት ወይም ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ውሳኔዎችን መስጠት ጥሩ አመራር ሊሆን አይችልም:: እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እምነት እንዳለን የሚያሳዩ ዕቅዶች እንዲኖሩን ይፈልጋል:: ነገር ግን እንድን ታላቅ ተግባር የሚፈጽምልን እግዚአብሔር እንጂ ዕቅዶቻችን አለመሆናቸውን መረዳት አለብን:: (ምሳሌ 19:21ን እንብብ::) እግዚአብሔር ራእዩንና ዕቅዶቹን እንዲገልጥልን እንጠይቀዋለን:: እንድናደርግ የሚፈልገውን ለማከናወን ተግተን እንድንሠራ የሚያስችለን ለመሆኑ ጥርጥር ሊገባን አይገባም:: ጳውሎስ እንዳለው፣ ምንም እንኳን ሙሉ ኃይላችንን ተጠቅመን መሥራት ቢኖርብንም፣ በእኛ ውስጥ «መሻትንም ማድረግንም» የሚሠራው እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: (ፊልጵ. 2:13ን እንብብ::)

እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚሰጡትን ጊዜና ገንዘብ በመጠቀም የማይቻሉ የሚመስሉትን ነገሮች ያደርጋል:: ነገር ግን ቤተ



ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ የማትቀበል ከሆነ፣ ያች ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን በረከት ልታገኝ አትችልም:: እግዚአብሔር የሚባርከው ሕዝቡ በእርሱ ላይ እምነት ሲኖራቸውና ሲታዘዙት ነው::

ይህ ማለት መሪዎችና ምእመናን እግዚአብሔር አንድን ነገር እንድናደርግ እንደ ተናገረና እየመራን ለመሆኑ ፍጹም እርግጠኞች መሆን አለብን ማለት ነው:: ራእዩ የሰው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር አሳብ መሆኑን ካላወቅን፣ ራሳችንን ሙሉ ለሙሉ ለራእዩ አሳልፈን ልንሰጥ አንችልም:: ለመሪዎች በግምት አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለቱ የራስ ወዳድነት ተግባር ነው:: እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ዕቅዶችን ለመባረክ ቃል አልገባም:: በራስ ወዳድነት ፍላጎቶች ተጀምረው ያልተጠናቀቁ (ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለአንድ ጎሳ ክብር ለማምጣት ሲባል) ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች አሉ:: ችግሩ የእግዚአብሔር ወይም የሕዝቡ እምነት-እልባነት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑ ነው:: ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ እምነትን ይጠይቃል:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ግልጽ ትእዛዝ ሳናገኝ እንድን ታላቅ ተግባር ብንጀምር፣ ይህ ግምት እንጂ እምነት አይደለም:: አይሁዶች የጋይን ከተማ ባጠቁ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነበሩ:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠይቁ የራሳቸውን ዕቅዶች አውጥተው ወደ ጦርነቱ ገቡ:: በውጤቱ ግን ከፍተኛ ሽንፈት ገጥሟቸዋል (ኢያሱ 7:2-5)::

15ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች ዝግጁ ባልሆኑት ምእመናን ላይ ራእያቸውን ሲጭኑ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ውጤቱ ምን ነበር? ለ) መሪዎችና ምእመናን ራእዩ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያዘጋጀው ነው ብለው የተስማሙበትን ሁኔታ ግለጽ:: ምእመናን የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በማወቃቸው ምን ተከሰተ? ሐ) አብዛኞቹ መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን ራእይ በመወሰኑ በኩል ምእመናንን የማያሳትፉት ለምንድን ነው?

**12. መሪዎችና ምእመናን የእግዚአብሔርን ራእይ እውን ለማድረግ በመሥዋዕትነት ራሳቸውን አሳልፈው መስጠት አለባቸው::**

መሪዎችና ምእመናን እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ መወሰናቸው በቂ አይደለም:: መሪዎችና ምእመናን ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን ካልሰጡ፣ ራእዩ እውን ሊሆን አይችልም:: እግዚአብሔር ለሙሴ ሕዝቡ ያመልክው ዘንድ የመገናኛ ድንኳን እንዲሠራ አሳየው:: ነገር ግን ራእዩ እውን እንዲሆን ሕዝቡ ገንዘብ መስጠትና የመገናኛውን ድንኳን በመገንባቱ ሥራ ላይ መሳተፍ ነበረባቸው:: እግዚአብሔር ለኢያሱና ለእስራኤል የከነዓንን ምድር ለመስጠት ቃል ገባ:: ይህም ሆኖ ሕዝቡ ወደ ከነዓን በመግባት ከግዙፍ ሰዎች ጋር መዋጋት ነበረባቸው:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ወንጌሉን ወደ ዓለም ሁሉ እንድትወስድ ከማዘዙም በላይ፣ «የገሃነም ደጆች እንደማይቋቋሟት» ተናግሯል:: ነገር ግን ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ እምነታችንን ለጎረቤቶቻችን ማካፈል፣ ለወንጌላውያን ደመወዝ እንዲከፈል ገንዘባችንን የመስጠትና ለምስክርነት ለሚወጡ አገልጋዮች የመጸለይ ኃላፊነት አለብን:: ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ራእይ ለመፈጸም ተሳትፎ ካላደረገችና ለጌታችን ለኢየሱስ ካልሠራን፣ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ ልትዳረስ አትችልም:: በተመሳሳይ መንገድ፣ መሪዎችና ምእመናን ለተግባራዊነቱ ራሳቸውን ካልሰጡ፣ የትኛውም ራእይ እውን ሊሆን አይችልም:: መሪዎችና ምእመናን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ካወቁ በኋላ፣ በታዛዥነት ለመመላለስ ራሳቸውን መስጠት አለባቸው::

ይሁንና፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእምነት በሚታዘዝበት ጊዜ ብቻችንን እንዳልሆንን ማወቁ ተገቢ ነው፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው:: እግዚአብሔር ለአይሁዶች ግዙፎቹን ሰዎች «እንዲወጉ» ቢነግራቸውም፣ እርሱም እንደሚዋጋላቸው ገልጾላቸዋል (ዘዳግ. 31:1-8):: እግዚአብሔር ለእርሱ እንድንመሰክር ወደ ዓለም ሁሉ ልኮናል (የሐዋ. 1:8):: ነገር ግን እርሱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር እንደ ሆነም ቃል ገብቶልናል (ማቴ. 28:20)::



እግዚአብሔር ራእይ በሚሰጠን ጊዜ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል ስጦታም ይሰጠናል:: ሥራውን ከፍጻሜ ለማድረስ እርሱ በእኛ ውስጥና በእኛ አማካኝነት ይሠራል::

16ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችሁ የሰጠውን የረዥም ጊዜ ራእይ ግለጽ:: ለ) ምእመናን በራእዩ ተግባራዊነት ላይ የተሳተፉት እንዴት ነበር? ሐ) ራእዩን ለመፈጸም እንድትችል እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ለመስጠት ቃል የገባው ምንድን ነው? መ) ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእዮች የማይፈጽሙት ለምን ይመስልሃል?

## ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእዮች የማይፈጽሙት ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር ለእያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን እርሱን የምታገለግልበትን ራእይና ራእዩን የምትፈጽምበትን ኃይል ከሰጠ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ለእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን የማያደርጉት ለምንድን ነው? ለዚህ ሁለት ዐበይት ምክንያቶች አሉ::

በመጀመሪያ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር እንዲያከናውኑ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ስለማያውቁ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው በሰጠው ራእይ ውስጥ አይሳተፉም:: ምእመናን በየእሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ያመልኩና ተመልሰው ይሄዳሉ:: ነገር ግን በማኅበረሰባቸው ውስጥ ለእግዚአብሔር ታላቅ ተግባር ለማከናወን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረው አይሠሩም:: ለዚህ ነው መሪዎች ምእመናን የእግዚአብሔርን ራእይ እንዲያውቁ መምራታቸው አስፈላጊ የሚሆነው::

ሁለተኛ፣ ለእግዚአብሔር መመስከርና መሥራት እንዳለባቸው እያወቁ ለዚህ ተግባር የሚያስፈልገውን መሥዋዕትነት ለመክፈል የማይፈልጉ ምእመናን አሉ:: ኢየሱስ በደቀ መዝሙርነት እርሱን መከተል መስቀል መሸከምን እንደሚያስከትል ተናግሯል (ሉቃስ 14:25-33):: ይህም ኢየሱስን መከተልና የእግዚአብሔርን ራእይ ለመፈጸም መሥራት ቀላል እንደማይሆን ያሳያል:: ሀብታም፣

በትምህርት የገፋን ወይም ታዋቂ ለመሆን ያለንን ፍላጎት መተው አለብን ማለት ነው። ከዚህ ይልቅ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት መሻት አለብን (ማቴ. 6:33)። ጊዜያችንንና ገንዘባችንን ለመስጠት ፈቃደኞች መሆን አለብን። ለዎች ሲስቁብን፣ ቤተ ለቦቻችን ወይም ጓደኞቻችን ሲቃወሙን፣ መታገሥ አለብን ማለት ነው። ይህ «መስቀል» ብዙውን ጊዜ ለሰዎች ከባድ ነገር ነው። ኢየሱስን የተቀበሉት ደኅንነትን፣ ቁሳዊ ሀብትን፣ አካላዊ ጤናን ስለሚሰጣቸው ነው። ነገር ግን የክርስቶስን መስቀል ለመሸከምም ይሁን በእስቻጋሪና መሥዋዕትነትን በሚጠይቁ መንገዶች ላይ ክርስቶስን ለመከተል እልተዘጋጁም። (ፊልጵ. 1:29ን አንብብ።) ራእዩ ጥሩ እንደ ሆነ በቃላቸው ቢስማሙም፣ አኗኗራቸውን ቀይረው ለራእዩ ተፈጻሚነት እንዳይሠሩ የግል ፍላጎቶቻቸው ያግዷቸዋል። ኢየሱስ በዘሪው ምሳሌ ላይ እንደ ጠቀለው ዘር፣ እነዚህም ራእዮች በግል ጉዳዮች አረሞች ታንቀዋል (ተከብበዋል) (ማቴ. 13:20-22)።

እንተስ እንዴት ነህ? እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግብህ ታውቃለህ? እግዚአብሔር የሚጠይቅብህን ነገር ለማድረግ እንድትችል ቃሉን ለማጥናት ጊዜ እየወሰድክ ነው? ወይስ ኢየሱስን ያለመከተል፣ መስቀልህን ያለመሸከምና እርሱ እንድታደርግ የሚፈልገውን ተግባር ያለማከናወን ችግሮች አሉብህ? ለምን አስቀድመህ «የእግዚአብሔርን መንግሥት» እንዳልፈለግክና ራእዩን ለመፈጸም እንደማትሠራ መንፈስ ቅዱስ እንዲገልጥልህ አሁኑኑ ጠይቅ። ከዚያም እግዚአብሔር ራስህን በመካድ በየትኛውም መንገድ ላይ እንድትከተለው እንዲረዳህ ጠይቀው።

## ሦስተኛ ቀን

## ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው የእግዚአብሔርን ራእይ እንዴት መረዳት እንዳለባቸው የሚገልጽ ማጠቃለያ

ይህ ለመረዳት የሚከብድ እሳብ ስለሆነ፣ መሪዎች ለአጭርና ረዥም ጊዜ አገልግሎቶች የእግዚአብሔርን ራእይ የሚቀበሉበት ሂደት ከዚህ በታች በአስተዋጽኦ መልክ ቀርቧል።



የእግዚአብሔርን ራእይ ለመረዳት በምንሞክርበት ጊዜ፣ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችሉትን ደረጃዎች ወይም ዕቅዶች ሳይሆን፣ መጨረሻው ላይ ሥራው ሲጠናቀቅ ምን ዓይነት ውጤቶች እንደሚኖሩ በዓይነ ሕሊናችን እንደምንመለከት ማስታወስ ይኖርብሃል። በሚቀጥለው ሳምንት ራእዩን እውን ለማድረግ እንዴት ጥሩ ዕቅዶች መንደፍ እንዳለብን እናጠናለን። መጀመሪያ ወዴት እንደምንሄድ ማወቅ አለብን። ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወን የምንፈልገውን የአገልግሎት ራእይ መረዳት አለብን።

## 1. ደረጃ አንድ:- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች የረዥም ጊዜ ራእዮች አዘጋጁ

ሀ. መሪዎች ለቤተ ክርስቲያኒቱ የእግዚአብሔር የረዥም ጊዜ ራእይ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ በቂ ጊዜ ሊመድቡ (ቢያንስ እራት ሰዓታት) እና በየጊዜው (ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ) ሊሰባሰቡ ይገባል። ይህን ለማድረግ ጊዜ ካልመደብን፣ በአጭር ጊዜ ችግሮችና ትናንሽ ራእዮች ላይ በማተኮር እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ለመግለጥ የሚፈልገውን እጅግ አስፈላጊ የረዥም ጊዜ ራእይ ቸል ልንል እንችላለን። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ፈቃድ ለማወቅ ጥረት በምናደርግበት ጊዜ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አንጻር ማብራሪያ የሚሰጥ እንግዳ ልንጋብዝ እንችላለን። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ራእይ እንዲገልጥልን በቡድን ሆነን ልንጸልይ እንችላለን። ከዚያም እሳቦቻችንን እያነሣን መወያየት አለብን።

ለ. መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ በመጀመሪያ፣ «ለቤተ ክርስቲያናችን ትልቁ የእግዚአብሔር ራእይ ምንድን ነው?» ብለን መጠየቅ አለብን። በመጀመሪያዎቹ ስብሰባዎች ላይ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ካገኘን፣ በየጊዜው ጉዳዩን እያነሣን ሁላችንም እግዚአብሔር የሚፈልገውን ትልቅ ራእይ እንዳንዘነጋ ማስታወስ አለብን። በውይይቱ መጨረሻ ላይ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን አጠቃላይ ራእይ በጽሑፍ ማስፈሩ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ ያህል ጽሑፉ፣ «እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው፣ ለክርስቶስ በመመስከርና ጉዳት ለደ

ረሰባቸው ወገኖች ፍቅራቸውን በማሳየት እያደጉ የሚሄዱ አማኞች የሚገኙባት የፍቅር ማኅበረሰብ እንድትሆን ይፈልጋል» የሚል ሊሆን ይችላል። (ራእይን በጽሑፍ ስለ ማስፈር ከታች የቀረበውን አሳብ ተመልከት።)

ሐ. በአመዛኙ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ከሚፈልገው ደረጃ ላይ ለመድረስ እንዴት እያደገች እንዳለ መወያየቱ መልካም ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠንካራ ጎኖች ምን ምንድን ናቸው? ደካማ ጎኖቿስ? ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ያሳየችባቸው አቅጣጫዎች የትኞቹ ናቸው? ባለችበት የቆየችባቸው ወይም ወደ ኋላ የተጓዘችባቸው አቅጣጫዎችስ? ቤተ ክርስቲያን ሆን ብላ ፈቃዱን ባለመፈጸሟ እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅና መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን በመምሰል እንድታድግ እንዲረዳት መጠየቁ ተገቢ ነው።

መ. መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ትልቁ ራእይ ነው ብለው የሚያምኑትን በንዑሳን ምድቦች መከፋፈል አለባቸው። ዋና ዋና አገልግሎቶችን ሳይመለከቱ እንዴት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ከሚፈልገው ደረጃ ልትደርስ እንደምትችል ማወቁ አስቸጋሪ ነው። እያንዳንዱ አገልግሎት የየራሱ ራእይ ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ ያህል፣ ከቤተ ክርስቲያን ዐበይት አገልግሎቶች አንዱ የወንጌል ስርጭት ነው። ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስርጭት ምን ራእይ ሊኖራት ይገባል? የዚህ ጥያቄ ምላሽ በሚከተለው መንገድ ሊገለጽ ይችላል፦ «እያንዳንዱ አማኝ ስለ ወንጌሉ ምንነት ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖረውና ይህንኑ ወንጌል በትጋት ለሌሎች እንዲያካፍል እንፈልጋለን። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ወንጌሉን ላልሰሙት እንዲያደርሱ የጠራቸው አገልጋዮች ለመሄድ እንዲችሉ እያንዳንዱ አማኝ ገንዘቡን በልግስና መስጠት አለበት።» እንዲሁም ደግሞ እንደ አምልኮ፣ የማኅበረሰብ ሕይወት፣ ማስተማር፣ የተጎዱትን ሰዎች መርዳት የመሳሰሉ የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘርፎች አሉ። እነዚህ ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ሊጤኑና ራእይ ሊዘጋጅላቸው ይገባል። ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻልበት ሌላው አማራጭ የእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት



ራእይ ምን መሆን እንዳለበት በጋራ መወያየት ነው። ለምሳሌ፣ የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ራእይ ምንድን ነው? የዲያቆናት አገልግሎት ራእይ ምንድን ነው? በማኅበረሰቡ መካከል የሚካሄድ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ራእይስ? የቤተ ክርስቲያን የኤች አይቪ ኤድስ፣ የስፖርት፣ የመሪዎች ሥልጠና፣ ወዘተ. . . ራእይ ምንድን ነው?

(ማስታወሻ፦ ሽማግሌዎች በእነዚህ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ላይ የሚሠሩ ሰዎች ራእዩን የማዘጋጀቱ ሂደት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ቢያደርጓቸው መልካም ነው። ወንጌላውያን፣ መጋቢዎች፣ የልማት ሠራተኞች፣ የወጣቶች መሪዎች፣ የሴቶች መሪዎች፣ ኳየር፣ የሰንበት ትምህርት ኃላፊዎች፣ ወዘተ. . . በስጦታዎቻቸውና በሥልጠናዎቻቸው አካባቢ ቤተ ክርስቲያን ምን ምን ተግባራት ላይ መሳተፍ እንዳለባት መግለጽ አለባቸው። ይህ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ እንዲገነዘቡና ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ ያግዛቸዋል። አገልጋዮች አብረው መሥራታቸው፣ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች የበለጠ አስፈላጊዎች ነን ከሚል አሳብ እንዲላቀቁ ያግዛል። እንዲሁም ደግሞ አገልጋዮቹ ለየአገልግሎቶቻቸው ሽማግሌዎች የሚከልሏቸውን ዝርዝር ዕቅዶች እንዲያወጡ ያስችላቸዋል።)

ሠ. ሽማግሌዎች ምእመናን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ የሚወስኑበትንና የሚረዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው። ምእመናን ራእዩን ካልተረዱና ካልተቀበሉ፣ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። ምእመናንን ከተሰማሙበት በኋላ ይህ ራእይ በጽሑፍ ሊሰፍርና ሁሉም ሰው ሊያይ በሚችልበት ስፍራ ሊቀመጥ ይገባል። ይህም ምእመናን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኒቱን ወዴት እየመራት እንዳለ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። (ራእዩን መጻፍ ለምን አስፈላጊ እንደሚሆን ከታች ተጨማሪ አሳብ ቀርቧል።)

**2. ደረጃ ሁለት፡- እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ለሰጣት አገልግሎት ሁሉ የአጭር ጊዜ ራእዮችን አዘጋጁ፡፡**

ሁሉም መሪዎች የረዥም ጊዜ ራእይን በየጊዜው መከለስ አለባቸው፡፡ እንደ አውነቱ ከሆነ ግን፣ በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ አብዛኛውን ጊዜ የሚወስዱት በቅርብ ጊዜ ለሚከናወኑ ተግባራት የተዘጋጁት ዕቅዶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ የሽማግሌዎችና ዲያቆናት የሥልጠና ፕሮግራም ለማዘጋጀት፣ ኮንፍረንስ ለማካሄድ፣ ወይም ምእመናን በሙሉ በማኅበረሰቡ ውስጥ ለአንድ ቀን ምስክርነት እንዲሰጡ ልናቅድ እንችላለን፡፡ እያንዳንዱ አገልግሎት ግልጽ ራእይ ሊኖረው እና በአገልግሎቱ አማካኝነት ሽማግሌዎች ምን ተግባር ለማከናወን እንደሚፈልጉም በግልጽ መታወቅ አለበት፡፡ ሽማግሌዎች ዕቅዶችን በሚያወጡበት ጊዜ ሊከተሏቸው የሚገባቸው ሦስት ደረጃዎች አሉ፡-

ሀ. አገልግሎቱን ከሚከታተሉ ሰዎች ጋር በመተባበር፣ ሽማግሌዎች በአጭር ጊዜ አገልግሎት ምን ለማድረግ እንደሚፈልጉ መወሰን አለባቸው፡፡ እንበልና፣ ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለወንጌል ስርጭት ትኩረት የሚሰጥበት ቀን እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ፣ «በዚህ ዕለት የወንጌል ስርጭት ቀን ይሆናል» ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ መነሻው መሆን ያለበት የወንጌል ስርጭት ቀን ዓላማ ምን እንደሚሆን ተወያይቶ ከስምምነት ላይ መድረስ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ዓላማው «ሁለት ወንጌላውያንን ለመላክ የሚያስችል ገንዘብ ማሰባሰብ» ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ከሆነ፣ የዕለቱ ዐቢይ ዓላማ ምእመናን ገንዘብ እንዲሰጡ መቀስቀስ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ወይም ደግሞ ዓላማው በቀበሌያችን ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ ሰው ወንጌልን መመስከር ሊሆን ይችላል፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ይህ ከመጀመሪያው ራእይ የተለየ ስለሆነ፣ መሪዎች ማተኮር ያለባቸው ገንዘብ በማሰባሰቡ ላይ ሳይሆን፣ ነገር ግን ሕዝቡ ወጥቶ ለቀበሌው ነዋሪዎች እንዲመሰክሩ በማድረጉ ላይ ነው፡፡ ለአንድ አገልግሎት ምንም ዓይነት ዕቅድ ከመውጣቱ በፊት የአገልግሎቱ ዓላማ በግልጽ መታወቅ አለበት፡፡



ለ. መሪዎች የአጭር ጊዜ ራእዮችን በተመለከተ ከምእመናን ጋር መወያየት አለባቸው፡፡ ይህም የሥራው ተሳታፊ ዎች እንዲሆኑና እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ሊያደርግ ባለው ነገር ምእመናን ደስ እንዲሰኙ ያደርጋል፡፡

ሐ. ሽማግሌዎች የአገልግሎቱን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉትን ዕቅዶች አገልግሎቱን በቀጥታ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ላለባቸው ወገኖች በውክልና መስጠት አለባቸው፡፡ (በኋላ እንዴት ውክልና መስጠት እንደሚቻል እንማራለን፡፡)

መሪዎች መማር ያለባቸው አጅግ ጠቃሚ ክህሎት ማንኛ ውንም አገልግሎት በሚጀምሩበት ጊዜ ራእዩ ምን እንደ ሆነ ማወቅና ምን ለማድረግ እየሞከሩ እንደ ሆነ መገንዘብ ነው፡፡ **ለማከናወን ስለምንፈልገው ነገር ያለን ግንዛቤ ግልጽና ወጥነት ያለው ከሆነ፣ በቀላሉ ዕቅዶችን ልናወጣና እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ተግባራዊ ልናደርግ እንችላለን፡፡**

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ የእግዚአብሔር ዋንኛ ራእይ ምን እንደ ሆነ የሚያሳዩ ሦስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን ጻፍ፡፡ ከሦስቱ የትኛውን የበለጠ እንደምትወድና ለዚህም ምክንያትህ ምን እንደ ሆነ ግለጽ፡፡ ለ) ዋንኛውን ራእይ በዐበይት ክፍሎች ክፋፍል፡፡ እነዚህ የእግዚአብሔር ራእይ ተግባራዊ እንዲሆን መከናወን ያለባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ዐቢይ ክፍል ራእዩን ጻፍ፡፡ ሐ) ቤተ ክርስቲያን ልትሳተፍ የምትችልባቸውን ሦስት የአጭር ጊዜ አገልግሎቶች ዘርዝር፡፡ ለእያንዳንዱ የአጭር ጊዜ አገልግሎት ራእይ ጻፍ፡፡ በሳምንታዊ ስብሰባችሁ ወቅት እነዚህን አሳቦች ለሌሎች የቡድንህ አባላት ታካፍላለህ፡፡ |

**እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን የሰጠውን ራእይ መጻፍ ለምን ያስፈልጋል?**

መሪዎች ከሚጋፈጧቸው ፈተናዎች አንዱ ምእመናን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው በሰጠው ራእይ ላይ እንዲያተ ኩሩ ማድረግ ነው፡፡ መሪዎች በአጭር ጊዜ ራእዮች ተስበው አስፈላጊዎቹን የረዥም ጊዜ ራእዮች ሊዘነጉ ይችላሉ፡፡ ይህ አንድ ሰው ለአግሩና ለሚረግጠው መሬት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ምክንያት ቀና ብሎ በመመልከት የሚሄድበት መንገድ ትክክል

መሆኑን ለማወቅ ካለመቻሉ ጋር ይመሳሰላል:: ምንም እንኳን መሪ ዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስታወቂያ በሚናገሩበት ጊዜ ስለ ራእዩ ጠቀስ በማድረግ ሕዝቡ እንዳይረሱት ለማድረግ ቢጥሩም፣ ብዙ መሪዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና ዋና ራእዮች መጻፍ ጠቃሚ መሆኑን ተረድተዋል:: ይህ በጽሑፍ የሰፈረ ራእይ «የራእይ መግለጫ» በመባል ይታወቃል:: ይህ ምእመናንና መሪ ዎች እንዲያዩት ተደርጎ በግልጽ ቦታ ላይ የሚቀመጥ አጭርና ግልጽ አሳብ ነው:: ራእዩን ሁሉም ሰው ሊያየው በሚችልበት ቦታ ማስቀመጡ አያሌ ጥቅሞች አሉት፡-

1. ሰቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች መቀጠል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: መሪዎች ሲለወጡ ወይም ሰዎች በአገልግሎቶች ሲጠመዱ በቃል የታሰበ ራእይ በቀላሉ ሊዘነጋ ይችላል:: በጽሑፍ የሰፈ ረ ራእይ ረጅም ጊዜ የመቆየት ዕድል አለው:: መሪዎች ይመ ረጣሉ፣ እንደ ገና ከብዙ ዓመታት በኋላ ሌሎች መሪዎች ይመጣሉ:: አዳዲስ የተመረጡ መሪዎች እግዚአብሔር ቀደም ሲል እንዴት ቤተ ክርስቲያኒቱን እንደ መራት ካላወቁ፣ ቀደም ሲል ከነበሩት መሪዎች ጋር በአንድነትና በስምምነት ለመሥራት ይቸገራሉ:: ወይም ደግሞ በፍጥነት አዳዲስ ነገሮችን መሥራት በመጀመራቸው፣ የበፊቶቹ መሪዎች የደከሙባቸውን ነገሮች ሊደግሙ ወይም ሊያወድሙ ይችላሉ:: እግዚአብሔር የበፊቶቹ መሪዎችን እንደ መራቸው እስካመንን ድረስ፣ በቂ ምክንያት ከሌ ለን በስተቀር፣ እነርሱ ያዘጋጁትን ራእይ መቀጠል አለብን:: በተ ጨማሪም፣ መሪዎች ከጊዜ በኋላ ለምን የተወሰኑ ውሳኔዎች እንደ ተሳለፉ ይዘነጋሉ:: እግዚአብሔር ያንን ንዑስ ራእይ እንድንመርጥ ይፈልጋል ብለን ያመንነው ለምን ነበር? በዚህ ግብ ለማከናወን የፈለግነው ተግባር ምን ነበር? እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ዎችና መልሶቻቸው በጽሑፍ ካልሰፈሩ፣ ሰዎች ለማከናወን የምንፈልጋቸውን ነገሮችና ለምን እነዚህን ነገሮች ለማከናወን እንደምንፈልግ ይረሳሉ:: ይህ ግራ መጋባትን ስለሚያስከትል፣ መሪ ዎች እስከ ዛሬ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን በሰጣት ዕድገት ለመቀጠል ይቸገራሉ:: ይህም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች እንደ ሰከረ ሰው ወዲያና ወዲህ እንዲንገዳገዱ ያደርጋል::



2. እግዚአብሔር እንድናደርግ መርቶናል ብለን የምናምነውን ራእይ በምንጽፍበት ጊዜ፣ ራእዩ ይበልጥ እየጠራ ይመጣል:: መሪ ዎችና ምእመናን በትክክል ራእዩ ምን እንደ ሆነ ሲወያዩና በአጭሩ በጽሑፍ ሲያሰፍሩ፣ ሂደቱ መሪዎችና ምእመናን ራእዩ የሌላ ሰው ሳይሆን የራሳቸው እንደ ሆነ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል:: «አዎን፣ ለማድረግ የምንፈልገው ይህንን ነው:: እግዚአብሔር ሲያሳየን የነበ ረው ይህንኑ ነው» ይላሉ::

3. «አንድ አሳብና አንድ መንፈስ» መኖሩ (ፊልጵ. 2:2)፣ በሽማግሌዎች መካከል፣ እንዲሁም በሽማግሌዎችና በምእመናን መካከል አንድነትን ይፈጥራል:: አሁን ሁሉም ሰው ለአንድ ዓላማ ይሠራል:: እያንዳንዱ ሰው ስምምነት የተደረገበትን አሳብ በመመ ልከት የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ ከመጠራጠር ይቆጠባል:: አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ወደ ግቧ እንድትጓዝ እስካደ ረጉ ድረስ፣ ምእመናን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዕድገትና ለውጥ ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት ይደግፋሉ::

4. ራእዩን በጽሑፍ ካሰፈርን በኋላ፣ ራእዩን ተግባራዊ ለማድ ረግ የሚያስችሉ ዕቅዶች ማውጣቱ ቀላል ይሆናል:: በዕቅዶቻችን መዳሰስ ያለባቸውን የግቡን የተለያዩ ክፍሎች በትክክል ለመረዳት እንችላለን:: አንድ ወይም ሁለት ነገሮችን ብቻ ሳይሆን፣ ራእዩን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ነገሮች በሙሉ ለመወሰን ስለምንችል፣ ሚዛናዊነቱን የጠበቀ ዕቅድ ልናወጣ እንችላለን::

5. የተጻፈ ራእይ በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን እና እግዚአብሔር በምእመናን ሕይወት ውስጥ የሚሠራበትን ሁኔታ ልንገመግም እንችላለን:: እግዚአብሔር ወደ ሰጠን ራእይ በመጓዝ ላይ መሆናችንን፣ ባለንበት መቆማችንን ወይም ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ እያፈነገጥን መሆናችንን ለመረዳት እንችላለን:: የራእይ መግለጫ እግዚአብሔር እንዴት እንድናድግ እንደሚፈልግ እንድናውቅ ይረዳናል:: ዕቅዶቹን በምናወጣበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር መሥራቱን የሚያመለክቱትን መረጃዎች ልናገኝ እንችላለን:: እግዚአብሔር አዳዲስ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲጨምር፣ እንዲሁም ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ሊረዳቸው

ይችላል:: ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በብስለት ማደጋቸውን ወይም እግዚአብሔር በመካከላቸው ምን እያደረገ እንዳለ አያውቁም:: በጽሑፍ የሰፈረ ግልጽ ራእይ መኖሩ እግዚአብሔር በመካከላችን እየሠራ መሆኑን እንድናውቅ ያስችለናል::

6. ሁሉም የተስማማበት የራእይ መግለጫ መኖሩ መሪዎች የትኞቹን አገልግሎቶች መደገፍ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ያሳያቸዋል:: በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ለውሳኔ የቀረቡትን ጉዳዮች በምንመለከትበት ጊዜ፣ ይህንን የራእይ መግለጫ በመመልከት፣ «ይህ ውሳኔ ራእያችንን ተግባራዊ ለማድረግ ሊያግዘን ይችላል ወይ?» ብለን እንጠይቃለን:: መልሱ «አያግዘንም» የሚል ከሆነ፣ በዚሁ መሠረት ሽማግሌዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚሰጡት ውሳኔ «አይሆንም» የሚል ይሆናል ማለት ነው::

7. ለምእመናን ሁሉ የሚታይ ራእይ መኖሩ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት እንደሚካሄዱና ሽማግሌዎች ለምን የተወሰኑ ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው ብለው እንደሚያምኑ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል:: እንዲሁም ደግሞ ምእመናን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የጸጋ ስጦታ በመጠቀም ለራእዩ ተግባራዊነት ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጡባቸውን መንገዶች እንዲያስቡ ያስችላቸዋል::

> 18ኛ ጥያቄ:- ሀ) ግልጽ ራእይ ለቤተ ክርስቲያን ማስተላለፍና ግቡን በጽሑፍ ማስፈር ለቤተ ክርስቲያን ዕቅድ ጠቃሚ የሚሆንባቸውን ሌሎች ምክንያቶች ዘርዝር:: ለ) ከራእይ መግለጫ ዓላማዎች አንዱ ምእመናን በሙሉ ቤተ ክርስቲያን ለማከናወን የምትፈልጋቸውን ነገሮች እንዲያውቁ ማገዝ ነው:: 1) ለአብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ መንገድ ማሰብና የራእይ መግለጫ መጻፍ ለምን ከባድ እንደሚሆንባቸው ግለጽ:: 2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጽሑፍ የሰፈረ ግልጽ ራእይ አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡ ምን ለውጥ መደረግ አለበት? 3) አብዛኞቹ ምእመናን ማንበብ የማይችሉ ከሆነ፣ መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ለማከናወን የምትፈልገውን ተግባር የሚያሳይ ግልጽ ራእይ በምእመናን አእምሮ ውስጥ ለማስረጽ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?



## የራእይ መግለጫ አጻጻፍ ማሳሰቢያ

ከላይ እንደ ተመለከትነው፣ እግዚአብሔር ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ያሳየንን ራእይ በጽሑፍ ማስፈርና ለሁሉም ሰው በሚታይ ቦታ ላይ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው:: እነዚህ አጫጭር የራእይ መግለጫዎች ጠቃሚ የሚሆኑት ለቤተ ክርስቲያን ዐበይት ግቦች ብቻ ሳይሆን፣ ለአያንዳንዱ ንዑስ ራእይ ወይም ንዑስ አገልግሎት ጭምር ነው:: አገልግሎቱ በጣም አጭር ዕድሜ ካለው (ለምሳሌ፣ ኮንፍረንስ)፣ የአገልግሎቱን ዓላማ የሚገልጽ ቀላል የቃል መግለጫ ብቻ ሊበቃ ይችላል:: ነገር ግን አገልግሎቱ ቀጣይነት ያለውና አስፈላጊ ከሆነ፣ ግቡ ላይ ለመወያየት በቂ ጊዜ ሊሰጥና ራእዩም ተጽፎ ለሁሉም በሚታይ ስፍራ መቀመጥ አለበት:: ጥሩ የራእይ መግለጫ የሚከተለውን ሊመስል ይገባል:-

**1. አጭር:-** ሰዎች አጫጭር ነገሮችን በቀላሉ ሊያስታውሱ ይችላሉ:: በራእይ መግለጫው ውስጥ ብዙ ነገሮች ከተዘረዘሩ፣ ሰዎች ስለ ራእዩ ግልጽ የሆነ አሳብ ለመጨበጥ ይቸገራሉ::

**2. ጠቅለል ያለ:-** ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ለማከናወን የምትሞክረውን ነገር እንዲያውቁ የራእይ መግለጫው ሙሉ መሆን አለበት:: መሪዎች (ወይም ምእመናን) አዲስ አገልግሎት ለመጀመር ከፈለጉ፣ የራእይ መግለጫውን በመመልከት ያሰቡት አገልግሎት እዚያ ውስጥ መኖሩን ያረጋግጣሉ:: ከሌለ፣ መሪዎች አገልግሎቱ የቤተ ክርስቲያን ተግባር አካል ሊሆን እንደማይችል ይወስናሉ፣ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ራእያቸውን እንዲያሰፉ እየጠየቃቸው እንደ ሆነ በማሰብ ግባቸውን ለመከለስ ይወስናሉ::

**3. ግልጽ:-** ሁሉም መሪዎችና ምእመናን ያለ ምንም ግራ መጋባት ወዲያውኑ ግቡን ለማወቅ እንዲችሉ የራእይ መግለጫ ቀላልና ግልጽ መሆን አለበት፣ ምእመናን ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ማጥናት ሳያስፈልጋቸው በቀላሉ ይረዱት ዘንድ በጥሩ ሁኔታ መጻፍ አለበት::

## የራእይ መግለጫ ምሳሌዎች

የቤተ ክርስቲያን ኮንፍረንስ የራእይ መግለጫ፡- *ራእያችን በዚህ ኮንፍረንስ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው የጸሎት ሕይወቱን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን በማሻሻል በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግ እንዲነሣሣ ማስቻል ነው።* በዚህ አጭር የራእይ መግለጫ አማካኝነት የተላለፈውን መልእክት ተመልከት፡፡ በመጀመሪያ፣ የኮንፍረንሱ ተጠቃሚዎች የማያምኑ ሰዎች ሳይሆኑ አማኞች ናቸው፡፡ ሁለተኛ፣ የኮንፍረንሱ ዓላማ አማኞች ጸሎትንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በመጠቀም በመንፈሳዊ ብስለታቸው እንዲያድጉ ማገዝ መሆኑ ተገልጾአል፡፡ ሦስተኛ፣ ለዚህ ኮንፍረንስ ምን ዓይነት ተናጋሪዎችን መጋበዝ እንዳለብን ይመራናል፡፡ ለዚህ ኮንፍረንስ ታዋቂ የፌውስ አገልጋይ ልንጋብዝ አንችልም፤ ምክንያቱም የኮንፍረንሱ ዓላማ ይኼ አይደለም፡፡ ነገር ግን አማኞች እንዴት ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስና የጸሎት ሕይወት ሊያዳብሩ እንደሚችሉ የማብራራት ብቃት ያለው ሰው መጋበዝ ይኖርብናል፡፡ አራተኛ፣ መሪዎች ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ በኮንፍረንሱ አማካኝነት ለአንድ ፕሮጀክት ገንዘብ ለማሰባሰብ ጥረት አናደርግም፤ ይልቁንም፣ ምእመናን እነዚህን ጠቃሚ መንፈሳዊ ተግባራት እንዲያከናውኑ የሚያግዟቸውን ነገሮች በማደራጀቱ ላይ እናተኩራለን፡፡ ሰዎች እነዚህን ጠቃሚ ርእሰ-ጉዳዮች የበለጠ እንዲረዱ ለማገዝ ስለ ጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተጻፉትን መጻሕፍት ልናቀርብላቸው እንችላለን፡፡ መሪዎች ማኅበረ ምእመኖቻቸውን እንዴት በመጽሐፍ ቅዱስና በጸሎት ቡድኖች እንደሚያደራጇቸው ልናሳያቸው እንችላለን፡፡ ይህ ኮንፍረንሱን የምናካሂድበትን ዓላማ የሚያስረዳው መግለጫ ብዙ ውሳኔዎችን እንድናካሂድ ያስችለናል፡፡

የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም የራእይ መግለጫ፡- *ራእያችን ከ5 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ እያንዳንዱ አባል የእግዚአብሔር ቃል ቀጣይነት ባለው መንገድ የሚቀርብበትና ሰዎች እንዴት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መኖር እንደሚቻል የሚማሩበት የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።* ይህ ቀላል መግለጫ ሽማግሌዎች የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም በሚጀምሩበት ጊዜ እንዴት እንደሚመሩቸው ተመልከት፡፡ በመጀመሪያ፣ የሰንበት ትምህርቱ ከ5 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ሁሉም ምእመናን በሚሳተፉበት መንገድ መዘጋጀት አለበት፡፡ በመሆኑም ለትናንሽ ልጆች፣ ለወጣቶችና ለአዋቂዎች የሚስማማ ትምህርት መቅረብ አለበት፡፡ ሁሉም ወይም አብዛኞቹ ምእመናን በዚህ ፕሮግራም ላይ ካልተሳተፉ፣ ራእዩ እንዳልተፈጸመ ይታወቃል፡፡ ሁለተኛ፣ ጽሑፉ ግባቸው ቀጣይነት ያለው ትምህርት እንደ ሆነ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም፣ የሰንበት ትምህርት መምህራን አስፈላጊ መሣሪያዎችን በማቅረብ የእግዚአብሔርን እውነት ለሁሉም በሚገባ መንገድ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሳምንታዊው ትምህርት አስተማሪው በሚፈልገው መንገድ የሚያቀርበው ብቻ ሳይሆን፣ በሚገባ የተደራጀ መሆን አለበት፡፡ ሦስተኛ፣ መሪዎችና የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ምን ዓይነት ትምህርት መስጠት እንዳለበት ይወስናሉ፡፡ ይህ ታሪኮች ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ብቻ የሚቀርቡበት ሊሆን አይገባም፡፡ ግቡ ሁሉም አማኞች አኗኗራቸውን እንዲቀይሩ ማገዝ ነው፡፡ ስለሆነም፣ የሚሰጠው ትምህርት ሰዎች አኗኗራቸውን በመቀየር ለእግዚአብሔር የበለጠ ክብር እንዲሰጡ የሚያነሣሣቸው መሆን አለበት፡፡

ከእነዚህ መግለጫዎች የትኛቹም «ምን» ለማድረግ እንደምንፈልግ አለመጥቀሳቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ይልቁንም፣ ራእዮቹ የሚናገሩት ምን ሲከሰት ለማየት እንደምንፈልግ ነው፡፡ በሥራው ውስጥ ግባችን ምን እንደሚሆን ይነግሩናል፡፡ ራእይ በሚቀጥለው ዓመት የምናከናውናቸውን ነገሮች የምንዘረዝርበት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እንዲፈጽም የምንፈልጋቸውን ነገሮች የሚያሳይ ነው፡፡ ለማከናወን የምንፈልጋቸው ነገሮች ዝርዝር የሚመጣው ከዕቅዳችን ሥር ነው፡፡ የምንሄድበትን ስፍራ ካላወቅን፣ ለማከናወን የምንፈልጋቸው ነገሮች ወደዚያው ያደርሱን እንደ ሆነ ለማወቅ እንቸገራለን፡፡ ዕቅዶቻችን ወደ ራእዩ ወይም ወደ ሌላ ቦታ እንደሚወስዱን ለማወቅ አንችልም፡፡

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በግል ሕይወትህ ውስጥ እንዲፈጸም የምትፈልገውን አንድ ነገር ምረጥ። (ለምሳሌ፣ ትምህርት፣ ቤት መሥራት፣ መንጃ ፈቃድ ማውጣት፣ የሙዚቃ መሣሪያ መማር፣ ወዘተ. . .) ራእይህን በመግለጽና ለምን ይህንን እንደምትፈልግ «የራእይ መግለጫ» ጻፍ። ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ልትሳተፍበት የምትፈልገውን አንድ አገልግሎት ምረጥ። እግዚአብሔር ከአሁኑ በበለጠ በአገልግሎቱ ይከብር ዘንድ ምን ለማድረግ እንዳሰባችሁ የሚያመለክት አሳብ የተካተተበት የራእይ መግለጫ ለዚህ አገልግሎት ጻፍ። አገልግሎቱ እንዲካሄድ «ለምን» እንደምትፈልግና ለእግዚአብሔር መንግሥት አስፈላጊነቱ ምን እንደ ሆነ ጻፍ።

## ለራሳችን ወይም ለቤተ ክርስቲያናችን ራእይን የምንወስንባቸው የተሳሳቱ መንገዶች

ግለሰቦችና አብያተ ክርስቲያናት ራእዮችን የሚያገኙት ከብዙ የተለያዩ ምንጮች ሲሆን፣ የሚጠቀሙትም ለተለያዩ ምክንያቶች ነው። ነገር ግን ራእዩ እግዚአብሔር የሰጠን ካልሆነ፣ በተሳሳቱ ዓላማዎች ላይ እየሠራን ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ሥራችንን እንዲያከብርና እንዲባርክ ከፈለግን፣ የያዝነው ራእይ የመነጨው ከእርሱ መሆን አለበት፤ እኛም ለትክክለኛ ምክንያቶች የእግዚአብሔር ራእይ ተሳታፊዎች መሆን አለብን። ከዚህ በታች ግለሰቦች ወይም አብያተ ክርስቲያናት ለተሳሳቱ ምክንያቶች የሚያከናውኗቸውና ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ተዘርዝረዋል፡-

*1. «<u>ይህ ሥራ መሠራት ስላለበት፣ እኛው መሥራት አለብን።</u>»* ብዙውን ጊዜ ለምን እንደምናደርግ ሳናውቅ ሥራውን ጀምረን እንገኛለን። ለምሳሌ፣ ለጎዳና ልጆች ስኬታማ አገልግሎት ስለሚሰጡ ሰዎች ስንሰማ፣ እኛም ለጎዳና ልጆች አገልግሎት እንጀምራለን። ወይም የስፖርት አገልግሎት እንጀምራለን። ነገር ግን እግዚአብሔር በግልጽ እንድናደርግ የሚፈልግ መሆኑን ካላወቅን፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያልሰጠውን ራእይ በመከተል ጉልበታችንን እናባክናለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ አገልግሎቶች ስኬታማ የማይሆኑት ሁሉም ይህ የእግዚአብሔር



ፈቃድ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ሳይደርሱ መሪዎች በፍጥነት ስለሚጀምሩ ነው።

እግዚአብሔር ለሁሉም ሰዎች ወይም አብያተ ክርስቲያናት አንድ ዓይነት አገልግሎት አይሰጥም። ለእኛና ለቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጣቸው ዕቅዶች ግልጽ ናቸው። መደረግ ያለበትን ሁሉ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ፣ እርሱ ለእኛ ያለውን ፈቃድ መፈለግ አለብን። እግዚአብሔር አንድ ቤተ ክርስቲያን የጎዳና ተዳዳሪ ልጆችን እንድትረዳ ሲመራና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ያንኑ አገልግሎት እንዲያካሂዱ ላይጠብቅ ይችላል።

አንድ ነገር አስፈላጊ ነው ማለት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር እንድናከናውናቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች ብቻ እንድናከናውን እግዚአብሔርን መስማት አለብን። ኢየሱስ በእስራኤል ወይም በዓለም ሁሉ ያሉትን በሽተኞች ለመፈወስ አልሞከረም። ይልቁንም፣ የፈወሰው እግዚአብሔር እንዲፈውስ የነገረውን ብቻ ነው። ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ እንዳጠናቀቀ ተናግሯል። (ዮሐ. 17:43 አንብብ።) ምንም እንኳን ብዙ ያልተከናውኑ ሥራዎች ቢኖሩም፣ የእርሱ ሥራ ተፈጽሞአል። በተመሳሳይ መንገድ፣ ሁልጊዜም እኛ ወይም ቤተ ክርስቲያናችን አሟልተን የማንጨርሳቸው ብዙ ችግሮች ይኖራሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ የወሰነው ሥራ ምን እንደ ሆነ በማሰብ ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ መልመድ አለብን።

*2. «የእነ እገሌ ቤተ እምነት እያደረገው ነው፣ ጥሩ ውጤትም እየገኙበት ነው፣ እኛም ማድረግ አለብን።»* በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት ብዙዎቹ ከሌሎች የሚኮረጁ ናቸው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ካካሄደች፣ እኛም ይህንኑ እንኮርጃለን። ወይም ደግሞ ማለፍያ ልብስ የለበሱ ብዙ መዘምራን ያሳት ቤተ ክርስቲያን ካየን፣ ያንንም እንፈልጋለን። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ራእይ እንደ አትሌቶች በውድድር ላይ መሆናችንን ያሳያል። ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለመወዳደር እየሞከርን ነው ማለት ነው። ቤተ

ክርስቲያን ግን የውድድር ሜዳ ልትሆን አይገባም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተሰብ የተለያዩ ባሕርያትና የአገልግሎት ዓይነቶች ያሏቸው ሁሉ የሰማዩ አባታችንን ለማስደሰትና ለማስከበር አብረው የሚሠሩባት መሆን አለባት፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን ራእይ መጠቀም እንጂ የሌሎችን መኮረጅ የለብንም፡፡

አንዳንድ ጊዜ ታዋቂ መጋቢዎች ሴሚናር በማካሄድ፣ «ልክ እኔ እንደማደርግ ካደረጋችሁ ውጤታማ ትሆናላችሁ» ይላሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልክ እርሱ እንዳደረገው ለማድረግ ይሞክሩና ሳይሳካላቸው ይቀራል፡፡ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች እንደሚሠራ ዘንግተዋል፡፡ እርሱ እንዱን ሰው ለመጠቀም የሚመርጥበት መንገድ ሌላውን ለመጠቀም ከሚመርጥበት የተለየ ነው፡፡ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የሚፈልገውና ከእኛ የሚፈልገውም አንድ ዓይነት ነገር ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ራእይ እንዲሰጡን ከምንፈልግ፣ እግዚአብሔር ራእይ እንዲሰጠን በቀጥታ ልንጠይቀው ይገባል፡፡

*3. «በዓለም ፊት መልካም ሆነን መታየት አለብን፡፡ ስለዚህ ነገሮችን በዚህ መንገድ ማካሄድ አለብን፡፡»* ለሌሎች በኬታማ መስለው ለመታየት በመፈለግ ውሳኔዎችን የሚሰጡ መሪዎች አሉ፡፡ «እኛ የባላገር ቤተ ክርስቲያን ተደርገን እየታየን ነው፡፡ ሰዎች እንዳይንቁን ብዙ የተማሩ ሰዎችን መሳብ አለብን!» የሚሉ አሉ፡፡ «እንዴት በሣር ቤት ውስጥ ልናመልክ እንችላለን? ሰዎች ምን ይሉናል? በሣር ቤት ውስጥ እስካለን ድረስ በክርስቶስ ለማመን አይችሉም፡፡» በማኅበረሰቡ ፊት መከበርን የመፈለጉ የራስ -ወዳድነት ፍላጎት ብዙዎች የተሳሳቱ ራእዮችን እንዲከተሉ አድርጓቸዋል፡፡ በማኅበረሰቡ ፊት የተከበርን መሆናችን ወይም በአገሪቱ ውስጥ ዝነኞች መሆናችን እግዚአብሔርን ብዙም አያሳስበውም፡፡ እርሱን የሚያሳስበው ስሙን የምናስከብር መሆናችንና ይህንንም የምናደርገው የቤተ ክርስቲያንን ውጫዊ ገጽታዎች ለመለወጥ ከመሞከር ይልቅ ልባችንን በመቀየር መሆኑ ነው፡፡



*4. «ገንዘብ ስላለን እናድርገው፡፡ የእርሱን የአሠለጣጠን መንገድ ከተከተልን፣ ለሥልጠና ፕሮግራሙ ገንዘብ የሚከፍል ለጋሽ ስላገኘን እናደርገዋለን፡፡»* መሪዎች በወቅቱ ገንዘብ በማግኘታቸው ብቻ አገልግሎት የሚጀምሩባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት መሪዎች ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለመሆኑን አይጠይቁም፡፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የረዥም ጊዜ አገልግሎት ይጠቅም ይሆን? ብለውም አይጠይቁም፡፡ ከሕዝቡ ባሕል ጋር መስማማቱም ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ መፈጸሙ አይጠየቅም፡፡ ገንዘቡ ስለ ተገኘ ብቻ አገልግሎቱ ይጀመራል፡፡

ብዙ መሪዎች እግዚአብሔር ከሚፈልገው ይልቅ (ይህ ማለት እንደ ድርጅት ያቀረበውን ገንዘብ አለመቀበልን የሚጨምር ቢሆንም እንኳ) ገንዘብ መገኘቱን እንደ መመዘኛ በመጠቀማቸው፣ ብዙ የእግዚአብሔር ሀብት ባክኗል፡፡ የረዥም ጊዜ ራእያችን አካል ያልሆነና አንድ ሰው ገንዘብ ይዞ በመምጣቱ ብቻ የተጀመረ አገልግሎት ገንዘቡ ሲያልቅ ይቆማል፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን ራእይ ካልሆነ፣ ሌሎች ሰዎች የሚፈልጉትን ዓላማ በማሳካት በቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ በብዙ ቦታዎች ከውጭ አገር ለጋሾች የሚመጣው ገንዘብ በሚቆምበት ጊዜ የልማት ሥራው ይቆማል፡፡ ማኅበረሰቦቻችንን መርዳት ልናደርግ የሚገባን የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ የገንዘብ ዕርዳታ ተገኘም አልተገኘም ሥራውን ማካሄድ አለብን፡፡ እንደ አቅማችን ለማኅበረሰባችን ፍቅራችንን ማሳየት መማር አለብን፡፡ ገንዘብ በመገኘቱ ብቻ ፈቃዱን ሳንጠይቅ የፕሮጀክት ሥራ ብናካሂድ፣ እግዚአብሔር ላባከንነው ገንዘብ ተጠያቂ አያደርገንም ይሆን? (አስታውሱ፣ ገንዘቡ የእግዚአብሔር እንጂ የለጋሹ አይደለም፡፡)

> **20ኛ** ጥያቄ፡- ሀ) መሪዎች ከእነዚህ የተሳሳቱ ምክንያቶች በአንዱ ተገፋፍተው አገልግሎት ሲጀምሩ ያየሀበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ችግሮችን እንዳስከተለ አብራራ፡፡

በዮሐንስ 10፡4 መልካም እረኛ ከመንጋው ፊት በመሄድ መንገድ እንደሚመራቸው ተገልጿል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናን እረኞች ናቸው፡፡ መንገዱን የመምራት ኃላፊነት

አለብን:: ነገር ግን መሄድ ያለብንን መንገድ የሚወስነው እግዚአብሔር ነው:: ስለሆነም እረኞች ማድረግ ያለባቸው የመጀመሪያው ተግባር ለመንጋው መሄጃ እግዚአብሔር የመረጠው መንገድ የትኛው ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ነው:: «መንገዱ» እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ራእይ ነው:: መሪዎችና ምእመናን በጋራ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያሰበውን ግብ መፈለግ አለባቸው:: «መንገዱ ይህ ነው:: በዚህ ሂዱ» (ኢሳ. 30:21) የሚለውን የእግዚአብሔር ድምጽ መስማት አለብን:: መሪዎች እንደ መሆናችን፣ በአመራር ውስጥ የመጀመሪ ያው ክህሎት ራእዩን እንዴት መወሰን እንደሚገባ ወይም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድትሄድ የሚፈልገውን መንገድ ማወቅ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ንዑሳን ራእዮች (ለምሳሌ፣ የሰንበት ትምህርት፣ የወንጌል ስርጭት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ፕሮግራም፣ የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም) ሁሉ የሚመራ አንድ ትልቅ ራእይ መኖር አለበት:: ትልቁን ራእይ ካወቅን በኋላ፣ ትናንሾቹን ግቦች ማወቁ ይቀላል:: እግዚአብሔር በሁሉም ግቦች ይክብር ዘንድ የተለያዩ ንዑሳን ራእዮችን ሚዛናዊ ማድረግም ይቀላል:: (ለምሳሌ፣ በወንጌል ስርጭት፣ ምእመናንን በማስተማርና ችግረኞችን በመርዳት መካከል ጤናማ ሚዛናዊነት ማድረግ::)

ራእይ ከሌለ ሕዝብ ይጠፋል (ምሳሌ 29:18):: ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት ራእይ ከሌሳት፣ በክርስቶስ አምነው ያልዳኑ ሰ ዎች ይጠፋሉ:: የምእመናንም መንፈሳዊ ሕይወትም ይጠፋል፣ ምክንያቱም ምእመናን እግዚአብሔር የሚፈልገውን እንዲሆኑ የሚያስችል ራእይ አልተነደፈምና:: በመጨረሻም፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ትሞታለች:: እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ልትማር የምትችለው ጠቃሚ ክህሎት ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ራእይ ምን እንደ ሆነ ማወቅና መወሰን መሆኑን አስታውስ:: በዚህ ሳምንት ለመሪዎችና ምእመናን የእግዚአብሔር ራእይና ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በመጠየቅና በመጸለይ ለምን የተወሰነ ጊዜ አታሳልፍም?



# አራተኛ ቀን

## ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ራእይ ምሳሌ (ሞዴል)

«እግዚአብሔር እንደ ቤተ ክርስቲያን ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?» ይህ መሪዎች ሊጠይቁት የሚገባ እጅግ አስፈላጊ ጥያቄ ነው:: ሽማግሌዎችና፣ በተለይም የሽማግሌዎች ሰብሳቢው፣ የቤተ ክርስቲያንን ራእይ የመወሰንና ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ራእዩን ለመፈጸም ጥረት እንዲያደርጉ የማነሣሣት ኃላፊነት አለበት:: አመራር ማለት ይኸው ነው::

ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የእግዚአብሔር ራእይ ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ የእግዚአብሔር ግብ ምን እንደ ሆነ ይነግረናል:: ይህ ራእይ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን ራእይ በምናዘጋጅበት ጊዜ ይመራናል:: ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዐቢይ ራእይና ንዑሳን ራእዮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እንመለከታለን::

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ኤፌ. 4:11-16 እና ቈላ. 1:28ን አንብብ:: እነዚህ ምንባቦች እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ስላለው ራእይ ምን ያስተምሩናል? ለ) እግዚአብሔር በሁሉም ቤተ ክርስቲያን ለማከናወን ይፈልጋል ብለህ ለምታስበው ተግባር «የራእይ መግለጫ» ጻፍ::

ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ራእይ ምን እንደ ሆነ መወሰን የሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ:: ኤፌ. 4:11-16 እና ቈላ. 1:28 በእኔ ግምት ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ራእይ ለመረዳት ግልጽ ምሳሌዎች ሊሰጡ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ስላለው ራእይ፣ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆንና ራእዩን የመፈጸሙ ውጤት ምን እንደሚሆን ከእነዚህ ጥቅሶች በዝርዝር እንማራለን::

**1. ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ራእይ ሲገልጽ (ኤፌ. 4:12-13):-**

ጳውሎስ እንደሚለው መሪዎችና ምእመናን ማድረግ ያለባቸው የሚከተለውን ነው:: *«ሁላችን (የቤተ ክርስቲያን አባላት) የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፣ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ::»* (በተጨማሪም፣ ቈላ. 1:28 አንብብ::) ጳውሎስ እግዚአብሔር ምእመናን ሁሉ መንፈሳዊ ብስለት እንዲኖራቸው እንደሚፈልግ ይገልጻል:: ምእመናን መንፈሳዊ ብስለትን ከሚያጎድልባቸው ነገር ሁሉ መራቅ አለባቸው:: መንፈሳዊ አለመብሰል አማኞች ስለ እምነታቸው ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አለማወቃቸውን ሊያመለክት ይችላል:: ይህ ከዘላለም አይታ አንጻር አምብዛም ትኩረት በማይሰጣቸው ነገሮች ላይ በአሳብ መከፋፈልን ያስከትላል:: በተጨማሪም፣ በመንፈሳዊ ሕይወት አለመብሰል ለእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚገባ አለመሥራትን ያመለክታል:: የትኛውም የመንፈሳዊ ብስለት ጉድለት መወገድ አለበት:: ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል የሚሆኑት ስለ እግዚአብሔር እውነቶችን በግልጽ ሲረዱና ለኢየሱስ ክርስቶስ ራሳቸውን አሳልፈው ሲሰጡ ነው:: መንፈሳዊ ብስለት ምእመናን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የቅርብ ግንኙነት ለማድረግ የመፈለጋቸው፣ በሕይወታቸው ኃይሉን የመለማመዳቸው እና ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ያለውን ፍቅር የማሳየታቸው ውጤት ነው:: (የጳውሎስን ጸሎት ከኤፌ. 3:16-19 አንብብ::) መንፈሳዊ ብስለት አለ የሚባለው የሰዎች ባሕርይና ሕይወት እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሲሆን ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሳሎች በምንሆንበት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን እንመስላለን::

22ኛ ጥያቄ:- ሀ) ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክት ውስጥ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያቀደው ራእይ ነው በማለት ከገለጸው አንጻር፣ ቤተ ክርስቲያናችሁ በሳል ነች ወይስ ያልበሰለች? መልስህን አብራራ:: ለ) ከላይ እንደተገለጸው፣ በሳል ለመሆን ቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ማድረግ ይኖርባታል?



**2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ወደ ብስለት እንድታድግ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው (ኤፌ. 4:11)::**

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ስጦታዎችና ኃላፊነቶች ያሏቸውን ብዙ ዓይነት መሪዎች ይዘረዝርና እነዚህ ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ይገልጻል:: እነዚህ መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን መቆጣጠር ወይም ማስተዳደር የለባቸውም:: ነገር ግን መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ወደ መንፈሳዊ ብስለት መምራት እንዳለባቸው ከእግዚአብሔር ቃል ተረድተናል:: እያንዳንዱ መሪ ጠቃሚ ሚና አለው:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንዲተከሉ ያደረጋቸው ሐዋርያት አሉ:: ይህም ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ከተከለበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው:: አዲስ ኪዳን ተጽፎ ከመጠናቀቁ በፊት የነቢይነትን ሚና በመጫወት ለሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር የማይለወጥ ፈቃድ እንዲናገሩ የተጠቀመባቸው አገልጋዮችም አሉ:: ወንጌላውያን ለዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው እንዲድኑ የሚመሰክሩ አገልጋዮች ናቸው:: እንደ መጋቢዎች/አስተማሪዎች ያሉ አንዳንድ መሪዎች አማኞች እምነታቸውን በመረዳት በመንፈሳዊ ባሕርይ እንዲያድጉ የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው:: (በትምህርት 21 ስለ እነዚህ የተለያዩ መሪዎች ኃላፊነቶች የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት::)

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ለማካሄድ ይችል ዘንድ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ልዩ ስጦታና ሚና እንዳለው መረዳቱ ተገቢ ነው:: ቤተ ክርስቲያንን የሚተክል ሰው ባይኖር፣ ቤተ ክርስቲያን ልትኖር አትችልም:: ላልዳኑት ሰዎች መልካሙን የምስራች የሚናገር ሰው ባይኖር፣ ወደ ብስለት የምናሳድጋቸው አማኞች አይኖሩም:: ሰዎች እንዴት ወደ እግዚአብሔር ጸጋ እንደሚያድጉ ወይም ስለ እግዚአብሔር እውነቶችን የሚያስተምር ሰው ባይኖር፣ መንፈሳዊ ብስለት ሊመጣ አይችልም:: ስለሆነም፣ እያንዳንዱ ዓይነት አገልጋይና መሪ እግዚአብሔር በሳል ቤተ ክርስቲያን ለማፍራት ባለው ራእይ

ውስጥ ጠቃሚ ሚና አለው:: በመሆኑም፣ እርስ በርሳችን ከመፎካከር ይልቅ፣ እያንዳንዱ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሌሎች አገልጋዮችን አስፈላጊነት በመገንዘብ እክብሮትና ማበረታቻ ሊሰጥ ይገባል:: ቤተ ክርስቲያን ጤናማ የመንፈሳዊ ብስለት ዕድገት ልታመጣ የምትችለው ሁሉም አገልጋዮች አብረው ሲሠሩ ብቻ ነው::

> **23ኛ ጥያቄ:-** ሀ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በአንድነት በመሥራት ቤተ ክርስቲያናቸውን ወደ መንፈሳዊ ብስለት የመምራት ኃላፊነት እንዳለባቸው የተገነዘቡ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ዓይነት መሪዎች ዘርዝር:: ምእመናን ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ በመርዳቱ በኩል እያንዳንዳቸው ምን ዓይነት ሚናዎችን ይጫወታሉ?

ቤተ ክርስቲያንን ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለመምራት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያደርጉት የሚገባ ሌላ ዐቢይ ነገር አለ:: ይህም ምእመናንን ማሠልጠንና የአገልግሎት ተሳታፊዎች ማድረግ ነው:: ጳውሎስ እነዚህ የተለያዩ ዓይነት መሪዎች *«የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት»* ከምእመናን ጋር አብረው መሥራት እንዳለባቸው ይናገራል:: ጤናማ ሰው ተግቶ ይሠራል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ክብር ተግታ ትሠራለች:: ስለዚህ፣ አገልጋዮች በምእመናን ፈንታ የቤተ ክርስቲያንን ሥራዎች የሚያካሂዱ አይሆኑም:: በመሆኑም፣ አገልጋዮች በሚሠሩበት ጊዜ እንኳን ምእመናንን በማሠልጠን ወንጌሉን ለጠፉት እንዲያካፍሉ ወይም ሌሎችን ወደ ብስለት እንዲመሩ ማስቻል አለባቸው::

> **24ኛ ጥያቄ:-** ሀ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በቀዳሚነት ትኩረት የሚያደርጉት ለምእመናን ሥራዎችን በማከናወን ላይ ነው ወይስ ምእመናንን በማሠልጠን አብረዋቸው እንዲሠሩ በማድረጉ ሥራ ላይ? መልስህን አብራራ:: ለ) አገልጋዮች የበለጠ ጊዜ ወስደው ምእመናንን በማሠልጠን አብረዋቸው እንዲያገለግሉ ቢያደርጉ ቤተ ክርስቲያን እንዴት የምትለወጥ ይመስልሃል? ሐ) አገልጋዮች ምእመናንን በማሠልጠን ለእግዚአብሔር ሥራ ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ የማይወስዱት ለምን ይመስልሃል?



3. ጳውሎስ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል በሚሆኑበት ጊዜ እያሌ ነገሮች እንደሚከሰቱ ገልጾአል (ኤፌ. 4:14-16):-

ሀ. በትጋት እግዚአብሔርን ያገለግላሉ:: እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ ሁሉ፣ ምእመናንም በምስክርነት፣ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በመምራት፣ አዳዲስ አማኞችን በማስተማር፣ ሌሎች አማኞችን በተለያዩ መንገዶች የሚረዱ፣ ወዘተ. . . ይሆናሉ:: እያንዳንዱ አማኝ መንፈስ ቅዱስ የሰጠውን ስጦታ በመጠቀም እግዚአብሔር የሰጠውን ተግባር ያከናውናል::

ለ. ምእመናን በእምነታቸው ይጸናሉ:: ብዙውን ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘልቀው በሚገቡ የተለያዩ ሐሰተኛ ወይም ሚዛናዊ ያልሆኑ ትምህርቶች አይወሰዱም:: ለራሳቸውና ለቤተ ክርስቲያን ከሁሉም የሚሻለው ምን እንደ ሆነ ሳያውቁ ከአንደኛው አዲስ ትምህርት ወደ ሌላኛው ሲሄዱ አይኖሩም::

ሐ. አንድነት ይኖራቸዋል:: በፊልጵ. 2:2 ጳውሎስ ይህ አንድነት *አንድ አሳብ፣ አንድ ፍቅር፣ በመንፈስና በዓላማ አንድ መሆን* ነው ይለናል:: እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድነት ሁልጊዜም ሁለት ነገሮችን ያካትታል:: በመጀመሪያ፣ እውነተኛነት ይኖራል:: ይህም ሁለት ገጽታዎች ያሉት ነው:: <u>አንደኛ</u>፣ እግዚአብሔር በቃሉ ካስተማረው ጋር የመስማማት እውነተኛነት ይኖራል:: እውነተኛ አንድነት ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ይመሠረታል:: ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆኑትን ነገሮች የሚያምኑና የሚተገብሩ ከሆነ (እንደ የይሖዋ ምስክሮች፣ ኢየሱስ ብቻ፣ ወዘተ. . . )፣ ከእንዲህ ዓይነት ሰዎች ጋር እውነተኛ አንድነት ሊኖረን አይችልም:: <u>ሁለተኛ</u>፣ እርስ በርሳችን እውነትና ትክክል የሆነውን ነገር መነጋገር አለብን:: ብዙዎቻችን ደካማ ጎኖቻችንን ስለማናውቅ፣ ድክመታችንን የሚነግረን ሰው ያስፈልገናል:: በመንፈሳዊ ሕይወታችን ልናድግ የምንችለው አንዳችን የሌላውን ድክመት በትክክል ስንጠቁም ብቻ ነው:: ይህ «ብረት ብረትን እንደሚስል» ማለት ነው (ምሳሌ 27:17)::

ሁለተኛ፣ **ፍቅር** ይኖራል። ፍቅር ለሌላው ሰው ከሁሉም የተሻለ ነገር መመኘት ነው። እንግዲህ ከመንፈሳዊ ብስለት በላይ ምን የተሻለ ነገር ይኖራል? ጳውሎስስ ቢሆን በጸሎቱ ትኩረት ያደረገው በዚሁ ጉዳይ ላይ አይደለምን? (ፊልጵ. 1:9-11፤ ኤፌ. 1:16-19፤ 3:14-19ን አንብብ።) እያንዳንዱ አማኝ ሌላውን በመውደድ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርስ ይረዳዋል። በብዙ ሰበዞች የተገመደ ገመድ በቀላሉ እንደማይበጠስ ሁሉ፣ አማኞች እርስ በርሳቸው እውነትን ሲናገሩ፣ አብረው ኅብረት ሲያደርጉ፣ እና አብረው ሲሠሩ፣ ጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስን የመከተል ጉዞአቸው የጠነከረ ይሆናል። (መክ. 4:12ን አንብብ።)

| |
|---|
| 25ኛ ጥያቄ፡- ቀደም ሲል የጻፍከውን የራእይ መግለጫ ከልስ። ከኤፌ. 4:11-16 በተማርነው መሠረት፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማድረግ ይፈልጋል ብለህ የምታስባቸውን ሌሎች ነገሮች በራእይ መግለጫህ ውስጥ ጨምር። |

ምእመኖቻችን የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርይ በማሳየት፣ በአገልግሎት ንቁ ተሳትፎ በማድረግና እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ ወደ መንፈሳዊ ብስለት በመጓዝ በሕይወታቸው ቢበረቱ፣ ይህ ምንኛ አስደሳች ነገር ነው! ሁላችንና እብያተ ክርስቲያኖቻችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመለስ ወይም እኛ እስክንሞት ድረስ ማደጋችንን መቀጠል አለብን። ይህ የመንፈሳዊ ዕድገት ሂደት ማብቂያ እንደሌለው እናውቃለን። ምናልባትም ለቤተ ክርስቲያን የራእይን መግለጫ እንደሚከተለው ጠቅለል አድርገን ልንጽፍ እንችላለን፡- *የእግዚአብሔር ራእይ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት አማኞች እርሱን በመንፈስና በእውነት በማምለክ፣ በእግዚአብሔር እውቀትና ከእርሱ ጋር ባላቸው ግንኙነት በማደግ፣ እያንዳንዳቸው ኢየሱስ ክርስቶስን በመምሰል በመንፈሳዊ ባሕርያቸው በመለወጥ፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያንና በዓለም የፍቅር አገልግሎት በመስጠት መንፈሳዊ ብስለት እንዲያሳዩ ነው።*

2. የበሳል ቤተ ክርስቲያን ንዑሳን ራእዮች።



ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን እውን ለማድረግ ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰዷ መልካም ነገር ነው። ነገር ግን በንዑሳን ክፍሎች ካልከፋፈልነው፣ እንዴት ራእዩን እውን ማድረግ እንደሚቻል ማወቁ አስቸጋሪ ነው።

ሚዛናዊ መንፈሳዊ ብስለት እንዲኖር ለማስቻል ማደግ ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ክፍሎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት፣ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ብስለት ምን እንደሚመስል ለማብራራት የሚረዱን በርካታ ንዑሳን ራእዮች አሉ።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብባቸው። መዝ. (29):2፤ (95):6፤ (99):9፤ ዮሐ. 4:23-24፤ ራእይ 7:9-12፤ ማቴ. 28:19-20፤ የሐዋ. 1:8፤ ሮሜ 10:14-15፤ ዘዳግ. 6:5-9፤ መዝ. (119)9፣11፤ ኤፌ. 5:27፤ 2ኛ ጢሞ. 2:15፤ 4:2፤ 1ኛ ጢሞ. 3:2፤ 1ኛ ቆሮ. 1:2፤ ፊልጵ. 1:9-11፤ 2ኛ ቆሮ. 11:2፤ ገላ. 6:2፤ 1ኛ ጢሞ. 6:18፤ ገላ. 2:10፤ ኢሳ. 58:5-8፤ ሚክ. 6:8፤ ማቴ. 25:31-46፤ ያዕ. 1:26-27። ሀ) ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የጠራትን ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እነዚህ ጥቅሶች ሊደረጉ ይገባል የሚሏቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) እነዚህን ነገሮች እንደየ ተመሳሳይነታቸው በምድብ ምድብ በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ ምድብ የራእይ መግለጫ ጻፍ። በራእይ መግለጫህ እግዚአብሔር ቢባርከውና ሕዝቡ በዚህ በኩል በሳል ሆነው ቢገኙ፣ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ግለጽ። |


ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ሁላችንም መንፈሳዊ ብስለት ያላት ቤተ ክርስቲያን ምን እንደምትመስል የየራሳችን እሳቦች አሉን። እንዲሁም ደግሞ ለዐቢይ ራእዩ መፈጸም ጠቃሚ የሆኑትን ንዑሳን ራእዮች ለመግለጽም የየራሳችን ምርጫዎች አሉን። ከዚህ በታች የቤተ ክርስቲያንን ዐቢይ ራእይ የሚገልጹ ንዑሳን ራእዮች የቀረቡበት አንድ ምሳሌ ተመልክቷል።

## የበሳል ቤተ ክርስቲያን አራቱ አዕማዶች

(ማስታወሻ፡- በዚህ ክፍል «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል የምንጠቀመው አዲስ ኪዳን ይህንን ቃል በሚጠቀምበት መንገድ ነው። በአዲስ ኪዳን ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የኢየሱስ ተከታዮችን እንጂ በፍጹም ሕንጻን አያመለክትም። ስለሆነም፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን

በምንነጋገርበት ጊዜ አብረው የሚያመልኩትን የሰዎች ቡድን ማመልከታችን ነው፡፡)

1ኛ ጴጥሮስ 2:5 አማኞች የእግዚአብሔር ቅዱስ ቤተ መቅደስ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው ይለናል፡፡ ሕያዋን ድንጋዮች ስለሆንን ደግሞ፣ ማደጋችንን ማቆም የለብንም፣ ቤተ ክርስቲያንም ከቶውንም መገንባቷን አታቆምም፡፡ በሙሪ እንጨት ተደግፎ የሚቆም የጭቃ ቤት ይሁን፣ ወይም ከሲሚንቶ የተገነባ የከተማ ቤት፣ ሁልጊዜም አንድ ቤት በሚሠራበት ጊዜ ቤቱን የሚሸከሙ አዕማዶች ያስፈልጋሉ፡፡ ጭቃው ወይም ጡቦቹ በምሰሶዎቹ ወይም በአዕማዶቹ መካከል ያሉትን ክፍት ቦታዎች ይሞላሉ እንጂ ቤቱን አይሸከሙም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መንፈሳዊ ቤታችን የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ሆና እንድትታይ የሚያስችሉ የተወሰኑ ነገሮች አሉ፡፡ ከዚህ በታች አራቱ የቤተ ክርስቲያን አዕማዶች ናቸው ብዬ የማስባቸው ነገሮች ተመልክተዋል፡፡ ከእነዚህ አንዱ ቢጎድል፣ ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ ልትሆን አትችልም፣ የኋላ ኋላም ለውድቀት ትዳረጋለች፡፡ እንዲሁም ደግሞ እያንዳንዱ አዕማድ እኩል መንፈሳዊ ሕንጻውን የማይሸከም ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ልትወድቅ ትችላለች፡፡






የመጀመሪያው አዕማድ የአምልኮ አዕማድ ነው፡፡ በብሉይና በአዲስ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ልጆቹ እርሱን እንዲያመልኩት አዝዟል፡፡ አንድ የቤተ ክርስቲያን ካትኪዝም፣ «ለምን ተፈጠርን?» የሚል ጥያቄ ያነሣና፣ «እግዚአብሔርን ለማምለክና ለዘላለም በእርሱ ደስ ለመሰኘት» የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ የመዝሙረ ዳዊት አብዛኛው ክፍል የተጻፈው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩት ለማገዝ ነው፡፡ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚፈልጉ ሰዎች በእውነትና በመንፈስ ሊያመልኩት እንደሚገባ ተናግሯል፡፡ ጳውሎስ መንፈሳዊ ማኅበረሰብ መዝሙሮችን በመዘመር የመንፈስ ቅዱስን ሙላት እንደሚያሳይ ተናግሯል፡፡ ጤናማ በሳል ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን የምታመልክ መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የአምልኮ ንዑስ ራእይ፣ *«በብስለት ጎዳና ላይ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ሁሉ ተሰባስበው እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት የሚያመልኩባት ናት»* የሚል ሊሆን ይችላል፡፡

**2ኛ ጥያቄ፡-** ሀ) አምልኮ በብስለት ጎዳና ላይ ላለች ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ነው ብለህ የምታስበው ለምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔርን ማምለክ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ምልክት መሆኑን የተገነዘብህበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ሐ) ቤተ ክርስቲያናችሁ የአምልኮ ፕሮግራሟን በመቀየር አምልኮው ይበልጥ በመንፈስና በእውነት እንዲካሄድ ልታደርግ የምትችልበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡

2. ሁለተኛው አዕማድ **የወንጌል ስርጭት** ነው፡፡ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርት ሁሉ የሰጠው የመጨረሻው ትእዛዝ ለስሙ እንዲመሰክሩ የሚጠይቅ ነበር፡፡ ሁላችንም ወንጌሉን ለዓለም በማስራጨቱ በኩል ተሳትፎ ማድረግ አለብን፡፡ የሐዋ. 1:8 የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ምን መምሰል እንዳለበት ያሳየናል፡፡ ምስክርነቱ የሚካሄደው ቤተ ክርስቲያኒቱ ባለችበት ማኅበረሰብ ውስጥ (ለምሳሌ፣ በኢየሩሳሌም)፣ በጎረቤት ቀበሌዎች (ለምሳሌ፣ በይሁዳ)፣ በጎረቤት ወረዳዎችና አውራጃዎች (ለምሳሌ፣ ሰማርያ) እና በዓለም ሁሉ ይሆናል፡፡ የማይመሰክሩ አማኞችና ክርስቲያኖች በብስለት እያደጉ አይደሉም፡፡ ምስክርነቷን ከራሷ ቀበሌ ወደ ጎረቤት ቀበሌዎች፣ አውራጃዎችና ዓለም ለማዳረስ ጥረት የማታደርግ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ጥሪ ተግባራዊ እያደረገች

አይደለችም፡፡ ስለሆነም፣ ለወንጌል ስርጭት የምንጽፈው ንዑስ ራእይ፣ «*በሳል ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ምእመናን ለጎረቤቶቻቸው እምነታቸውን የሚያካፍሉባትና ወኪሎቻቸውን እንደ ወንጌላውያን ወደ ጎረቤት አካባቢዎች በመላክ የወንጌል ስርጭት የሚያካሂዱባት፣ እንዲሁም እነዚህን ወንጌላውያን ለመደገፍ በልግስና የሚሰጡባት ነች*፡፡»

**28ኛ ጥያቄ፡-** ሀ) የወንጌል ስርጭት የበሳል ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ክፍል ነው ብለህ የምታምንበትን ሁኔታ አብራራ፡፡ ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ይህንን ንዑስ ራእይ ተግባራዊ እያደረገች ያለችው እንዴት ነው? ሐ) ይህንን ንዑስ ራእይ እንዴት በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ልታደርግ ትችላለች?

3. ሦስተኛው አዕማድ ማስተማር ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገው የማያምኑ ሰዎች እምነው እንዲድኑ ወይም እንደ መንፈሳዊ ልጆች ዳግም እንዲወለዱ ብቻ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹ በሙሉ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርሱ ይፈልጋል፡፡ (ሕጻን ልጁ ዕድሜ ልኩን ሕጻን ሆኖ እንዲቀር የሚፈልግ ወላጅ የለም፡፡) መጽሐፍ ቅዱስ ለአማኞች ሕይወትን የሚለውጥ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ሳያቋርጥ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር አይሁዶች የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር በሕይወታቸው ቀዳሚ ጉዳይ ማድረግ እንዳለባቸው አስጠንቅቋቸዋል፡፡ መዝሙረኛው ሰዎችን ንጹሕ የሚያደርገው የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት እንደ ሆነ ያስረዳል፡፡ ጳውሎስ መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት የማያሳፍር ሠራተኛ ሊሆኑ የሚችሉት የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ እንደ ሆነ ተናግሯል፡፡ እንዲያውም፣ በአዲስ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቅና ለሌሎች የማስተማር ብቃት የሌለው ሰው በሽምግልና አይመረጥም ነበር፡፡ ጳውሎስ አማኞች በእውቀትና በመረዳት እንዲያድጉ ጸልዮአል፡፡ ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያንን በሳል ለማድረግ ትምህርት ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ነገር ግን ማስተማር ማለት መረጃን መስጠት ብቻ አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ማስተማር ሰዎችን ወደ ኩራት ይወስዳል (1ኛ ቆሮ. 8፡1)፡፡ ይልቁንም፣ ማስተማር በሰዎች



ሕይወት ውስጥ የሚከተሉትን ለውጦች ለማምጣት የሚጠቅም መሣሪያ ነው፡-

ሀ. የአስተሳሰብ ለውጥ፡፡ በሮሜ 12፡1-2 አስተሳሰባችንን እንድንለውጥ ተነግሮናል፡፡ አስተሳሰባችን በሚለወጥበት ጊዜ፣ ባሕርያችንና አገልግሎታችን ይቀየራል፡፡ ብስለት የሚመጣው ክርስቲያኖች እንደ ዓለማውያን ማሰባቸውን ሲያቆሙና እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማሰብ ሲጀምሩ ነው፡፡

ለ. የባሕርይ ለውጥ፡፡ በሳል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በመንፈሳዊ ባሕርያቸው የሚያድጉባት ናት፡፡ አማኞች የክርስቶስን ባሕርይ እየተላበሱ ይሄዳሉ፡፡ በቅድስና፣ በፍቅር፣ ራስን በመቆጣጠርና በሌሎችም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ያድጋሉ፡፡

ሐ. ለእግዚአብሔር የተነቃቃ አገልግሎት ማካሄድ፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው፣ መሪዎች ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማካሄድ እንዲችሉ የሚያዘጋጁቸው በማስተማር ነው፡፡ መሪዎች ትኩረት መስጠት ካለባቸው ነገሮች አንዱ ምእመናን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ተግባር እንዲያከናውኑ ማሠልጠን ነው፡፡

እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማየት የሚፈልጋቸው ብዙዎቹ ነገሮች የማስተማር አገልግሎት ውጤቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር የማትጸልይን ቤተ ክርስቲያን በኃይል ለመጠቀም ይቸገራል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ጸሎት፣ ጾም የመሳሰሉ መንፈሳዊ ነገሮች የሚመጡት ከውጤታማ የማስተማር አገልግሎት ነው፡፡ በተጨማሪም ውጤታማ የማስተማር አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን በመጠቀም የሚያገለግሉ ሰዎችን ማፍራት አለበት፡፡

እንግዲህ የማስተማር ንዑስ ራእይ እንዴት ይገለጻል? «በሳል ቤተ ክርስቲያን የዕድሜ፣ የጾታ ወይም የትምህርት ልዩነት ሳይኖር፣ ምእመናን በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ እንዲያስቡ፣ በባሕርያቸው ክርስቶስን እንዲመስሉ፣ እንዲሁም

ለእርስ በርሳቸውና በአካባቢያቸው ላሉት አገልግሎት ያበረክቱ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል የተማሩ አማኞች የሚገኙባት ነች፡፡»

29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ማስተማር የበሳል ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የአገልግሎት ክፍል ነው ብለህ የምታስብበትን ምክንያት ግለጽ፡፡ ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ይህን ንዑስ ራእይ እንዴት ተግባራዊ እያደረገች እንደ ሆነ ግለጽ፡፡ ሐ) ይህ አዕማድ በቤተ ክርስቲያናችሁ የበለጠ ይጠናከር ዘንድ ምን ቢደረግ ጥሩ ነው?

አራተኛው አዕማድ ለሰዎች ክርስቲያናዊ ፍቅር ማሳየት ነው፡፡ ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን መጨረሻ ድረስ፣ እግዚአብሔር ለሰዎች ምሕረትንና ጸጋን እንድናሳይ፣ እንዲሁም የሕይወት ውጣ ውረድ ለደረሰባቸው ሰዎች እንክብካቤ እንድናደርግ ያዝዘናል፡፡ ለድሆች ፍቅርን ማሳየት ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በሕዝቡ ላይ ከተቆጣባቸው ምክንያቶች አንዱ ድሆችን ለመንከባከብ ባለመፈለጋቸው ነበር፡፡ እንዲያውም በፍትሕና በትክክለኛነት፣ ብሎም ችግር የደረሰባቸውን ሰዎች በመርዳት ካልተመላለሱ፣ አምልኮአቸው ከንቱ እንደ ሆነ ተናግሯል፡፡ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ሁሌም የታመሙትንና ድሆችን ያገለግል ነበር፡፡ ኢየሱስ ሰዎች ጉዳት በሚደርስባቸው ጊዜ በርኅራኄ እንደሚንቀሳቀስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል፡፡ እንዲያውም፣ ይህ ለእርሱ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በአንድ ምሳሌ ውስጥ ችግረኞችን ያልረዱ ሰዎች ራሱ ጌታን እንዳልረዱትና ወደ ሲኦል እንደሚሳኩ ተናግሯል፡፡ ክርስቶስ ሁለቱ እጅግ አስፈላጊ ትእዛዛት የትኞቹ እንደ ሆኑ ሲናገር፣ ሰዎች እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን ባልንጀሮቻቸውንም መውደድ እንዳለባቸው ተናግሯል፡፡ ድሆችን መርዳት ለቀድሞዎቹ አማኞች እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ይህ የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሊፈጽሙት የሚገባ ነው ብለው ትእዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡ ያዕቆብም እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሃይማኖት ድሆችን መርዳት መሆኑን ተናግሯል፡፡ ስለሆነም፣ ከቤተ ክርስቲያን ዐበይት አገልግሎቶች አንዱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በችግር ላይ ያሉትን ሰዎች መርዳት ሊሆን ይገባል፡፡



ምናልባትም ይህንን ንዑስ ራእይ እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል፡፡ *«በሳል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በማኅበረሰቡ ውስጥ ችግር ያለባቸውን ወገች ለመርዳት የክርስቶስን ፍቅር የሚያሳዩባት ናት፡፡»* እግዚአብሔር እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ሀብቷን ለወንጌል ስርጭትና ለማስተማር አገልግሎት እንድትጠቀም እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ድሆችንም እንድት ረዳ ይፈልጋል፡፡ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን ለጋሽ ሳትሆን በሳል ልትሆን አትችልም፡፡ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን ምእመኖቿ በለጋሽነት ሳይሰጡ ከውጭ አገር የሚመጣው ርዳታ ብቻ በማኅበ ረሰቧ ውስጥ ያለውን ችግር ይቀርፋል ብላ ማሰብ የለባትም፡፡ ፍቅር እውነተኛ ሊሆን የሚችለው ከራሳችን ሲመጣ ነው፡፡ ዳዊት ገንዘብ ያሳወጣሁበትን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አልሠዋም ብሎ ነበር (2ኛ ሳሙ. 24:24)፡፡ ለእግዚአብሔር የሰጠው ነገር ዋጋ ሊያስከፍለው የግድ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ለሌሎች ፍቅር ማሳየት የሆነ ዋጋ ሊያስወጣን ይገባል፡፡ ምንም ዋጋ ካላስወጣን፣ እውነተኛ ፍቅር እያሳየን ላይሆን ይችላል፡፡

30ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያናዊ ፍቅር ማሳየት የበሳል ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ክፍል የሚሆነው ለምን እንደ ሆነ አብራራ? ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ይህንን ንዑስ ራእይ እንዴት ተግባራዊ እያደረገች እንደ ሆነ ግለጽ፡፡ ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ይህ አዕማድ የበለጠ እንዲጠናከር ምን ቢደረግ ጥሩ ነው? መ) የበሳል ቤተ ክርስቲያን መገለጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ የምትላቸውን ሌሎች አዕማዶች ዘርዝር፡፡

አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች አዕማዶችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚፈልጋቸው አብዛኞቹ ነገሮች በእነዚህ አራት አዕማዶች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ መሪዎች እንደ መሆናችን፣ በእነዚህ በአራቱም ንዑሳን ራእዮች ሚዛናዊ የሆነች በሳል ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት መትጋት አለብን፡፡ እግዚአብሔርን በተነቃቃ መንፈስ የምታመልክ፣ ንቁ የወንጌል ስርጭት የምታካሂድ፣ ሰዎች በቅድስና፣ በጽድቅና ክርስቶስን በመምሰል ያድጉ ዘንድ ቃሉን በግልጽና ባለማቋረጥ የምታስተምር፣ እንዲሁም ለድሆች የምትራራ ቤተ ክርስቲያን ልትኖረን ይገባል፡፡ እነዚህ አራት አዕማዶች በአገልግሎታችን ውስጥ ካልተንጸባረቁ፣ ወይም

በገንዘብ አጠቃቀማችን እነዚህን አራት አዕማዶች ካላንጸባረቅን፣ ምናልባትም በሳልና ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ሳንሆን እንችላለን። እያንዳንዱ አማኝ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ በሳል አባል ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችሁ እነዚህን አራት ንዑሳን ራእዮች ሚዛናዊ አድርጋ እንድታካሂድ ይርዳት።

## አምስተኛ ቀን፡- ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የውይይት ጥያቄዎች፡-

1. ሀ) በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ ራእዮችና ዕቅዶች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዴት እየተካሄዱ እንደ ሆነ ግለጽ። ለ) ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ራእይ ለቤተ ክርስቲያን ለመወሰን ምን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ? ሐ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ወይም አገልግሎትን በመስጠት ላይ ያሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ራእይ ለቤተ ክርስቲያን ለመወሰን ምን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ? መ) ምእመናንስ?

2. ሀ) ብዙ የሽማግሌዎች ቦርዶች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ እንዲያከናውኑ የሚፈልጉትን ተግባር በተ መለከተ ራእይ የሌላቸው ለምንድን ነው? ለ) መሪዎች እንደ ቤተ ክርስቲያን የሚያከናውኗቸው ተግባራት በሁኔታዎች እንዲወሰኑ ከማድረግ ይልቅ በእግዚአብሔር ራእይ ለመመራት ይችሉ ዘንድ፣ ለቤተ ክርስያቲያን ዕቅድ ማውጣትን በተመለከተ ከመሪዎች ግንዛቤ ውስጥ መለወጥ ያለበት ምንድን ነው?

3. ሀ) ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣ ራእይን ስለ መወሰን የተማርናቸውን የተለያዩ አጠቃላይ ነገሮች ዘርዝር። ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእነዚህ እውነቶች መካከል ብዙውን ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የትኞቹ ናቸው? ሐ) ብዙውን ጊዜ ተግባራዊ የማያደርጓቸውስ የትኞቹ ናቸው? መሪዎቹ እነዚህን እውነቶች ተግባራዊ የማያደርጓቸው ለምንድን ነው? መ) እነዚህን እውነቶች ማወቅ ሽማግሌዎች የተሻሉ ራእይ ያላቸው መሪዎች እንዲሆኑ እንዴት እንደሚረዳ ግለጽ።

4. ሀ) በዐቢይ ራእይና በንዑሳን ራእዮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ለ) እያንዳንዱ ተማሪ ለ17ኛው ጥያቄ የጻፈውን መልስ ለቡድኑ ያካፍል። ከዚያ በኋላ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ የእግዚአብሔርን ትልቅ ራእይ የሚገልጸውን የተሻለ አጭር መግለጫ ምረጡ። ይህንን መግለጫ የመረጣችሁት ለምንድን ነው? ሐ) ከእነዚህ ንዑሳን ክፍሎች ውስጥ የእግዚአብሔር ራእይ እውን እንዲሆን መከናወን ያለባቸውን ዋና ዋና ነገሮች ከሁሉም በተሻለ መንገድ የሚገልጸው የትኛው ነው? ለእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ ወይም አገልግሎት ራእይ ይሆናል ብላችሁ የምታምኑትን መግለጫ በጋራ ጻፉ። መ) ቤተ ክርስቲያን ልታካሂድ የምትችላቸውን ሦስት የአጭር ጊዜ አገልግሎቶች ምረጡ። ለእያንዳንዱ የአጭር ጊዜ አገልግሎት ራእዩ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያስረዳ አጭር መግለጫ ጻፉ። ሠ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን ዐቢይ ራእይ እንዲረዱ ለማገዝ ምን እያደረገች ነው? ምእመናን ዐቢይ ራእይን እና ንዑሳን ራእዮችን እንዲገነዘቡና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎቶች ሚዛናዊነትን በጠበቀና ቅንጅት በፈጠረ መንገድ እንዲካሄዱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

5. ሀ) ለቤተ ክርስቲያን የጳውሎስ ዐቢይ ራእይ ምን ነበር? ለ) ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው? ሐ) ራእዩ ተግባራዊ እየሆነ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች ምን ምን ነበሩ? መ) ቤተ ክርስቲያናችሁን ከጳውሎስ ራእይ ጋር አነጻጽር። ቤተ ክርስቲያናችሁ ከጳውሎስ ራእይ ጋር ተመሳሳይና ጠንካራ የሆነችው በምን በኩል ነው? ደካማ የሆነችውስ? ሠ) ለለ በሳል ቤተ ክርስቲያን ከተገለጹት ንዑሳን ራእዮች ቤተ ክርስቲያናችሁ ጠንካራ የሆነችው በየትኞቹ ነው? ደካማ የሆነችውስ? ረ) ቤተ ክርስቲያናችሁ አራቱንም ንዑሳን ራእዮች ለማጠናከር ምን ማድረግ አለባት ትላለህ?